የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ

ጥቅምት 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ

ጥቅምት 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1
1.1 መግቢያ 1
1.2 ዓላማ 1
1.3 ዝርዝር ዓላማዎች 2
1.4 የተፈፃሚነት ወሰን 2
1.5 መርሆች 2
1.6 የቃላት ፍቺ (ትርጓሜ) 3
1.7 የጸታ አገላለጽ 3
1.8 አህጽሮተ ቃላትና አጫጭር ስያሜዎች 3
ክፍል ሁለት፡ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት 4
2.1. ሚኒስቴር /ፕሬዝዳንት/ ዋና ዳይሬክተር/ሥራ አስፈጻሚ/ ሥራ አስኪያጅ/ 5
2.2. የሳይበር ደህንነት ዳይሬክቶሬት/ዋና ክፍል/ 6
2.3. የሳይበር ደህንነት መሪ (Steering) ኮሚቴ 8
2.4. የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ቡድን (ክፍል) 9
2.5. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ቡድን (ክፍል) 11
2.6. የሳይበር ደህንነት ኢንጂነሪንግ ቡድን (ክፍል) 13
2.7. የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና ግምገማ ቡድን (ክፍል) 15
2.2. የሳይበር ደህንነት ክስተት ክትትል እና ምላሽ ቡድን (ክፍል) 17
ክፍል ሶስት፡ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት የሥራ መደቦች 19
3.1. የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ቡድን (ክፍል) የሥራ መደቦች 20
3.2. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ቡድን (ክፍል) የሥራ መደቦች 40
3.3. የሳይበር ደህንነት ኢንጂነሪንግ የሥራ ቡድን (ክፍል) መደቦች 63
3.4. የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና ግምገማ ቡድን (ክፍል) የሥራ መደቦች 78
3.5. የሳይበር ደህንነት ክስተት ክትትል እና ምላሽ ቡድን (ክፍል) 96
ክፍል አራት፡ የማዕቀፉ አተገባበር 127
4.1. ማዕቀፉን ከተቋማት አውድ ጋር ስለማጣጣም 127
4.2. በማዕቀፉ አተገባበር ወቅት ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች 128
4.3. ስለማዕቀፉ አተገባበር 128
4.4. የማዕቀፉ አለመፈጸም የሚያስከትለው ተጠያቂነት 129
4.5. ማዕቀፉን ስለማሻሻል 129
አባሪዎች 129

ክፍል አንድ

1.1 መግቢያ

አሁን ባለንበት ዘመን የተቋማትን መረጃዎች፣ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችንና ስርዓቶችን ከሳይበር ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት መከላከል የሚያስችል አቅም መገንባት የተቋማትን ብሎም የሃገርን የሳይበር ደህንነት ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት አስፈላጊ ነው።

የሳይበር ደህንነት አቅም በተቋማት እና በሀገር ደረጃ ለመገንባት፤ እንዲሁም ከሳይበር ምህዳር የተገኙ እድሎችን ለመጠቀም እንዲያስችል የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት መዘርጋት እና ለመዋቅሩ የሚመጥን እውቀትና ክህሎት ያላቸው አመራሮችንና ባለሙያዎችን መፍጠር የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ አስቻይ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። አደረጃጀቱ እና የሥራ መደብ መዋቅሩ የሃገራችንን የሳይበር ደህንነት ራዕይና ተልዕኮዎች ለማሳካት መሰረታዊ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ በመሆኑ በሁሉም የመንግስትና ቁልፍ የግል ተቋማት ውስጥ ለመዘርጋት እንዲያስችል ሆኖ ተዘጋጅቷል።

ስለሆነም ሰነዱ የሳይበር ደህንነትን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል የተቋማትን አውዳዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በሁሉም የመንግስት እና የግል ቁልፍ ተቋማት ውስጥ የሚተገበር አደረጃጀት እና የሥራ መደብ መዋቅር የያዘ ነው።

በመሆኑም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲን(ኢመደኤ) እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 808/2006 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ ሊዘጋጅ ችሏል።

1.2 ዓላማ

በሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን፣ የመረጃ መሰረተ-ልማቶችንና ስርዓቶችን ከሳይበር ስጋት፣ ተጋላጭነት እና ጥቃት ለመከላከል፣ እንዲሁም የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተቋማትንና የሀገርን አውድ ያገናዘበ አደረጃጀት እና የሥራ መደብ መዋቅር እንዲኖር ለማስቻል፤

1.3 ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ. በተቋማት ደረጃ ግልጽ የሆነ የሳይበር ደህንነት የሥራ ድርሻ እና ኃላፊነትን ለይቶ ለማስቀመጥ፤

ለ. የተቋማትን መረጃዎች፣ የመረጃ መሰረተ ልማቶች እና የመረጃ ስርዓቶችን ደህንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል፤

ሐ. ከሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንዳርዶች እና ህጎች ጋር የተጣጣመ አደረጃጀት በተለያዩ ተቋማት እንዲኖር ለማድረግ፤

1.4 የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ በሃገሪቱ በሚገኙ በሁሉም የመንግስት እና ቁልፍ የግል ተቋማት ውስጥ የተቋማቱን ዓውድ ባገናዘበ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

1.5 መርሆች

እነዚህን መርሆች እንደመነሻ በመጠቀም ተቋማት የራሳቸውን ተልዕኮና አውድ ባገናዘበ ሁኔታ ሌሎች መርሆችን ማካተት ይችላሉ፡፡ ይህ ማዕቀፍ የሚከተሉትን መርሆዎች ታሳቢ ያደርጋል፡፡

ሀ. ተጠያቂነት፡- ይህ ማዕቀፍ በሚተገበርባቸው ሁሉም ተቋማት ውስጥ በመዋቅሩ የተመደበ አመራርም ሆነ ባለሙያ የሚሰጣቸውን ተግባራት በተጠያቂነት ይፈጽማሉ፡፡

ለ. ኃላፊነት፡- በዚህ አደረጃጀት የሚመደቡ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ የማወቅ፣ የመቆጣጠር፣ ሚናቸውን የመለየት እና የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

ሐ. አውዳዊነት፡- ይህ ማዕቀፍ ውጤታማ እንዲሆንና የታለመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የተቋማትን ራዕይና ተልዕኮ ባገናዘበ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

መ. ቅንጅትና አጋርነት፡- የሳይበር ደህንነትን ማረጋገጥ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ሁሉም በዚህ ማዕቀፍ የተጠቀሱ አደረጃጀቶች ከሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በአጋርነት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

1.6 የቃላት ፍቺ (ትርጓሜ)

ቁልፍ የመረጃ መሰረተ-ልማት ማለት በሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ፤ በባህሪው ለሳይበር ጥቃትና ስጋት ተጋላጭ የሆነና በሚደርስበት ጥቃትም ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሰረተ ልማት ነው።

የመረጃ ስርዓት ማለት በተቋማት ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀት፣ ለማከማቸትና በተቀናጀ ሁኔታ በዕውቀት ለመጠቀም የሚያስችሉ ስርዓቶችን፣ እንዲሁም ስርዓቶቹን ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያችል ገዢ ሰነዶችን (ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንደርዶች፣ ፕሮግራሞች፣...ወዘተ) ያካትታል።

የመወዳደሪያ አቅም ማለት አመራሩና ባለሙያው የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ተግባር በአግባቡ ለመወጣት የሚያስፈልጋቸው ብቃት ነው።

የሳይበር ምህዳር ማለት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ መረጃዎች፣ የመረጃ መሰረተ ልማቶች፣ መረጃ ስርዓቶች፣ መረጃን ወደ እውቀት የሚቀይርና የሚጠቀም የሰው ሃይል፤ እንዲሁም ተቋማዊና ማህበረሰባዊ ባህል ያካተተ ምህዳር ነው።

ሳይበር ደህንነት ማለት በሳይበር ምህዳር የተፈጠሩ አስቻይ ስርዓቶችን ከተለያዩ የሳይበር ስጋቶች፣ተጋላጭነቶችና ጥቃቶች በመከላከል ሀብቶችን፣ የአሰራር ሂደቶችንና መዋቅሮችን በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ መጠቀም ነው።

የሳይበር ጥቃት ማለት በሳይበር ምህዳር የሚፈጸም ያለፈቃድ ብርበራ፣ የመረጃ ስርቆት፣ ቫይረሶችን ማሰራጨት፣ ስነ ልቦናዊ ጦርነት እና ሌሎችም መሰል የሳይበር ጥቃቶችን ያካትታል።

የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ማለት የሳይበር ደህንነትን ለመምራት፣ ለማስተዳደርና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሰነድ ነው።

1.7 የጾታ አገላለጽ

ማንኛውም በዚህ ማዕቀፍ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፤

1.8 አህጽሮተ ቃላትና አጫጭር ስያሜዎች

ኢመደኤ፡ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ

ኢኮቴ፡ ኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ

ክፍል ሁለት፡ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት

ይህ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተቋማትን አውድ ባገናዘበ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆን ነው፡፡ አደረጃጀቱ ከሚኒስቴር/ፕሬዝዳንት/ዋና ዳይሬክተር/ሥራ አስፈጻሚ/ እስከ ባለሙያ ድረስ ያለውን የሚያካትት ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ አደረጃጀቶች ተግባርና ኃላፊነት በግልፅ ለማስቀመጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም አደረጃጀቱ እንደአስፈላጊነቱ ተቋማት ከራሳቸው አውድ አንጻር በመመልከት ተግባራዊ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡



ስዕል 0 1፡ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት

2.1. ሚኒስቴር /ፕሬዝዳንት/ ዋና ዳይሬክተር/ሥራ አስፈጻሚ/ ሥራ አስኪያጅ/

አጭር መግለጫ

የተቋሙን የሳይበር ደህንነት በበላይነት የሚመራ፣ የሚያስተዳድር፣ ከተቋሙ ተልዕኮ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ስትራቴጂክ ዕይታዎችን በመከተል በኃላፊነት አቅጣጫ የሚያስቀምጥ አካል ነው። የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት ዓላማውን እንዲያሳካ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ አቅም በመገንባት እና ውጤታማነትን በማረጋገጥ በሥሩ ካሉ ክፍሎች ጋር ይሰራል። እንዲሁም የሳይበር ደህንነትን አስመልክቶ የተቀረጹ አዳዲስ ፕሮግራሞችን ኃላፊነት በመውሰድ በጀት በመመደብ ተግባራዊ ያደርጋል። በመሆኑም ሚኒስትር/ፕሬዝዳት/ዋና ዳይሬክተር/ሥራ አስፈጻሚ/ሥራ አስኪያጅ/ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባሮችና እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

ዋና ዋና ተግባሮችና ኃላፊነቶች

ሀ. የሳይበር ደህንነት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅትን በበላይነት ይመራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ለ. በተቋሙ የሳይበር ደህንነት አሰራር ስርዓት መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤

ሐ. ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንዳርዶችና ሌሎች ህግጋት በተቋሙ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤

መ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና መመሪያዎች ውጤታማነት ያረጋግጣል፤

ሠ. የሳይበር ደህንነት መለኪያዎች መቀመጣቸውን ያረጋግጣል፤እንዲሁም በመለኪያዎቹ መሰረት እንዲከናወን አቅጣጫ ይሰጣል፤

ረ. የሳይበር ደህንነት ስቲሪንግ ኮሚቴን በበላይነት ይመራል፤

ሰ. የሳይበር ደህንነት ቁጥጥር /ኦዲት/ ሪፖርት በመገምገም አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

ሸ. ዓመታዊ የሳይበር ደህንነት የሥራ ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ያቀርባል፤

2.2. የሳይበር ደህንነት ዳይሬክቶሬት/ዋና ክፍል/

አጭር መግለጫ

ይህ ዳይሬክቶሬት/ዋና ክፍል/ የተቋሙን የሳይበር ደህንነት የሚመራና የሚያስተዳድር የሥራ ክፍል ነው። የሳይበር ደህንነት መመሪያዎች እና ፕሮግራሞች መቅረጽና ማስተዳደር፣ እንዲሁም አዳዲስ አስተማማኝ የደህንነት መፍትሄዎችን ከማዘጋጀት ባሻገር የተቋሙን የሳይበር ደህንነት በአስተማማኝ መልኩ ማስተዳደር ነው። ዳይሬክቶሬቱ/ዋና ክፍሉ/ የተቋሙን የመረጃ ሃብቶች ምስጢራዊነት፣ ምልዑነት እና ተደራሽነት በሚመለከት ፖሊሲዎችንና ሂደቶችን የመምራት እና የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት። በመሆኑም ዋና ዋና ተግባር እና ኃላፊነት በሚከተለው መልኩ የተዘረዘረ ሲሆን ሌሎች መስፈርቶች (ዕውቀት፣ ክህሎት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሰርተፍኬት እና የመወዳደሪያ አቅሞች ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 1 እና 2) ተደርገዋል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ዝግጅትን ይመራል፤

ለ. ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ መነሻ በማድረግ የተቋሙን የሳይበር ደህንነት አመራር ስርዓት ያጎለብታል፣ በየሁለት ዓመቱ እንዲከለስ ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ. የሳይበር ደህንነት መመሪያዎችን እና አሰራሮችን /ፕሮሲጀሮችን/ ያፀድቃል፤

መ. የሳይበር የደህንነት ስትራቴጂዎችን እና ስርዓቶችን በማቀናጀት እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

ሠ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎችና ፕሮሲጀሮችን ውጤታማነት በየጊዜው ይፈትሻል፣ ይገመግማል፣ ያረጋግጣል፤

ረ. የሳይበር ደህንነት አመራር ስርዓት አፈጻጸምን ይገመግማል፤

ሰ. አዳዲስ የሳይበር ስጋቶችን እና ተጋላጭነቶችን ለመለየት የሚያስችል ዓመታዊ እና መደበኛ የሳይበር ደህንነት ክስተት ዳሰሳ (risk assessment) ያደርጋል፤ አዳዲስ ስጋቶችንና ተጋላጭነቶችን ለመቀነስ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል፤

ሸ. የመረጃ ስርዓቶች አገልግሎት ከመስጠታቸው በፊት የሳይበር ደህንነት ክፍተት ዳሰሳና ትንተና ውጤት ከተቀመጠው የደህንነት ክፍተት ትንተና መስፈርት ጋር በማመሳከር የስጋት ደረጃ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤

ቀ. በሳይበር ደህንነት ዙሪያ በተቋማት መካከል ቅንጅትና ትብብር እንዲፈጠር እና እንዲጠናከር አስተዋጽኦ ያደርጋል፤

2.3. የሳይበር ደህንነት መሪ (Steering) ኮሚቴ

አጭር መግለጫ

የሳይበር ደህንነት መሪ (Steering) ኮሚቴ ለዘርፉ ቀረቤታ ካላቸው ዳይሬክቶሬቶች /የሥራ ክፍሎች/ በሚወከሉ አካላት ይዋቀራል። መሪ ኮሚቴው በተቋም ውስጥ የሳይበር ደህንነት እሳቤ በግልጽ እና ሁሉን አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲከናወን በተቋሙ ሲታመንበት ይቋቋማል። በመሆኑም ኮሚቴው የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል። ከዚህ በተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ የመወዳደሪያ አቅሞቹ /Competency/ ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 3) ተደርጓል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት የሥራ ዕቅድ ያዳብራል፣ አፈጻጸም ይከታተላል፤

ለ. የተቋሙ የሥራ ክፍሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶች አጠቃቀም በሳይበር ደህንነት እሳቤዎች መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ሐ. የሳይበር ደህንነት ስጋት መቀነሻ ስትራቴጂ እንዲቀረጽ የሚመለከተውን አካል ያስተባብራል፣ ስትራቴጂውን ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የሳይበር ደህንነት ፕሮጀክቶችንና ተግባራትን በመለየት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፤

መ. የሳይበር ደህንነት ፕሮጀክቶች ትግበራ ላይ ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ ያስተባብራል፤

ሠ. የሳይበር ደህንነት አስተዳደር /ማኔጅመንት/ ስርዓትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤

ረ. ታክቲካል የሳይበር ደህንነት የአደጋ/ስጋት/ ዳሰሳ በየስድስት ወሩ ያከናውናል፤ የአደጋ/ስጋት/ ፕሮፋይል ያዘጋጃል፤

ሰ. ለኢንፎርሜሽን ስርዓት ዕውቅና ሰጪ ባለስልጣን የቴክኖሎጂና ስርዓት ደህንነት ፍተሻ መደረጉን በማረጋገጥ የአደጋ/ስጋት/ ደረጃ ተቀባይነት ያለው መሆኑን በመገምገም የኢንፎርሜሽን ስርዓቱ አካል እንዲሆን ይፈቅዳል፣ እውቅና ይሰጣል፤

ሰ. በሳይበር ደህንነት ላይ የሚሰራና ወሳኝ የሆኑ የመረጃ ስርዓቶችን ለሚያስተዳድር ሰራተኛ የይለፍ ፈቃድ (security clearance) መሰጠቱን ያረጋግጣል፤

ሸ. ማንኛውም የሳይበር ጥቃት፣ የፖሊሲና ፕሮሲጀር ጥሰቶችና አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ለሳይበር ደህንነት ዳይሬክቶሬት ያሳውቃል፣ ሪፖርት ያቀርባል፤

2.4. የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ቡድን (ክፍል)

አጭር መግለጫ

የሳይበር ደህንነት አስተዳዳር ቡድን (ክፍል) በዋነኝነት የተቋሙን ስጋት አስተዳደር መነሻ በማድረግ የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች (ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎች፣ ሞዴሎች፣ ሜትዶሎጂ፣ ማዕቀፎች) በማበልፀግ በስርዓት እንዲመራ ማድረግ ነው። እንዲሁም የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች ከሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች ጋር እንዲጣጣም በማድረግ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ በመስኩ ተቋማዊ አቅም መፍጠር ነው። በመሆኑም የቡድኑ (የክፍሉ) ዋና ዋና ተግባር እና ኃላፊነት እንደሚከተለው የተገለጸ ሲሆን የሥራ መደቦች ዝርዝር ደግሞ በዚህ ሰነድ ክፍል ሶስት ተዘርዝረዋል። በተጨማሪም የሥራ ቡድኑ /ክፍሉ/ መሪ ሊኖሩት የሚገቡ የመወዳደሪያ አቅሞች ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 4) ተደርጓል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ተልዕኮዎችን ከፖለቲካዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከማህበራዊ እና ከህጋዊ ፍላጎቶች፣ እንዲሁም ከሥራ ባህል ፍልስፍና፣ ከአለም-አቀፍ ቴክኖሎጂያዊና ከሌሎች አውዳዊ ጉዳዮች አንጻር በመገንዘብና በመተንተን ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ. ተቋማዊ ተዕዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎች፣ ስታንዳርዶች፣ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎች፣ ሞዴሎች፣ አስተሳሰቦች እና ማዕቀፎች ያበለጽጋል፤

ሐ. የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች በተቋም ውስጥ እንዲተገበሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፤

መ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ለመምራት የሚያስችሉ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል ይተገብራል፣ ይመራል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በየሁለት ዓመቱ ይከልሳል፤

ሠ. በተቀረጹ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶች ላይ የምክክር መድረኮች ያዘጋጃል፣ ይመራል፣ ያቀናጃል፤

ረ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት የስራ ቀጣይነት አስተዳደር ፕሮግራምና እቅድ (Business continuity plan) ይቀርፃል፣ ይዘረጋል፤

ሰ. የአደጋ/የስጋት ማገገሚያ እቅድ እና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ይከታተላል፤

ሸ. በመረጃ፣ በመረጃ ስርዓት እና በመረጃ መሰረተ ልማት ላይ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት እሳቤዎች ከሃገሪቱ ህጎችና ደንቦች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

ቀ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ገዢ ሰነዶች በተመለከተ ለሳይበር ደህንነት ትምህርት/ስልጠና/ ወይም ንቃተ ህሊና ክፍል ስልጠና ፕሮግራም ይቀርፃል፣ የስልጠና ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

2.5. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ቡድን (ክፍል)

አጭር መግለጫ

የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ቡድን(ክፍል) በእውቀት፣ በአመለካከት እና በተግባር ማነስ ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነትና ጥቃት በመገንዘብ የሚሰራ ነው። በሳይበር ደህንነት ዋንኛው ተጋላጭ እና በየትኛውም የሳይበር ደህንነት ፕሮግራም ውስጥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው የመከላከያ መስመር የሰው ሃይል መሆኑን በመረዳት ለሳይበር ደህንነት ባለሙዎች እና አመራሮች፤ እንዲሁም ለተቋሙ ሰራተኞች የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ በማሰተባበር ይሰጣል። በተጨማሪም በተቋም ውስጥ የሳይበር ደህንነት ባህል እና መሰረታዊ እሳቤዎች እንዲጎለብቱ እና በሰው ሃይል ክፍተት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የሳይበር ጥቃት እና አደጋ በመቀነስ በመስኩ ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ማድረግ ነው። በመሆኑም የቡድኑ (የክፍሉ) ዋና ዋና ተግባር እና ኃላፊነት እንደሚከተለው የተገለጸ ሲሆን የሥራ መደቦቹ ዝርዝር ተግባራት ደግሞ በዚህ ሰነድ ክፍል ሶስት ተዘርዝሯል። እንዲሁም የሥራ ቡድኑ(ክፍሉ) መሪ ሊኖሩት የሚገቡ የመወዳደሪያ አቅሞች ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 5) ተደርጓል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ፕሮግራም ይቀርፃል፤ ያዘጋጃል፤ ይመራል፤

ለ. የሳይበር ደህንነት አመራር እና ባለሙያ የሳይበር ደህንነትን ለመምራት የሚያስችል ንቃተ ህሊና እንዳላቸው ቀጣይነት ባለው መንገድ ያረጋግጣል፤

ሐ. የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ፕሮግራም ስርዓት ንድፍ በማዘጋጀት እና በመተግበር ለአመራሩና ለባለሙያው የሳይበር ደህንነት ዕውቀት ሽግግር ያደርጋል፤

መ. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊናና አቅም ግንባታ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶች፣ ማዕቀፎች፣ አጀንዳዎች፣ ጽንሰ ሀሳቦች...ወ.ዘ.ተ ያለማል፤

ሠ. የስጋት አስተዳደር ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ ያቀናጃል፤ እንዲሁም በዘርፉ ተቋማዊ አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፤

ረ. በሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎች፣ ፕሮሲጀሮችና ገዢ ሰነዶች ላይ ስልጠና ይሰጣል፤

ሰ. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ባህል በተቋም ውስጥ እንዲፈጠር እና እንዲያድግ ያደርጋል፤

ሸ. የተቋሙ ሰራተኞች ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤና ንቃተ ህሊና ደረጃ እና የሳይበር ደህንነት ባህልን አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ያከናውናል፣ ይገመግማል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

ቀ. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ሪፖርቶችን ያጠናቅራል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያቀርባል፤

2.6. የሳይበር ደህንነት ኢንጂነሪንግ ቡድን (ክፍል)

አጭር መግለጫ

የሳይበር ደህንነት ኢንጂነሪንግ ቡድን (ክፍል) በዋነኛነት የተቋሙን ተልዕኮ ለመደገፍ በተዘረጉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች እና ስርዓቶች ላይ የደህንነት ስጋት እንዳይከሰት የመከላከል፣ የመከታተል፣ የመቆጣጠር እና በየጊዜው አዳዲስ ለውጦችን የማሻሻል ኃላፊነት አለበት። በተቋሙ ፖሊሲ መነሻ የስርዓቶችን ተደራሽነት የሚቆጣጠር እና የሚፈቅድ ይሆናል። እንዲሁም ያልተፈቀዱ ሙከራዎችን ይመረምራል፣ የሳይበር ደህንነት መሳሪያዎችን ያስተዳድራል፣ ለውጥ ያደርጋል፣ ኮንፊገር ያስማማል፣ የደህንነት ክፍተት መዝጊያዎችን (Security patch) እየተከታተለ ያድሳል። በመሆኑም ቡድኑ (ክፍሉ) የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች የሚኖሩት ሲሆን የሥራ መደቦቹ ዝርዝር ተግባራት ደግሞ በዚህ ሰነድ ክፍል ሶስት ተዘርዝሯል። በተጨማሪም የሥራ ቡድን /ክፍል/ መሪ ሊኖሩት የሚገቡ የመወዳደሪያ አቅሞች ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 6) ተደርጓል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. በተቋሙ ውስጥ ስራ ላይ በሚገኙና በአዳዲስ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪዎች ላይ አስፈላጊውን የደህንነት እርምጃ ይወስዳል፤

ለ. የቴክኖሎጂዎችን ደህንነት በቀጣይነት ሳይቋረጥ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

ሐ. የሳይበር ደህንነት ኢንጂነሪንግ ፕሮጀክቶች በሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲዎች እና ማዕቀፎች መሰረት መሰራታቸውን ያረጋግጣል፤

መ. የተቋሙ የሳይበር ደህንነት ስርዓት ከሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ስርዓት ጋር ተናባቢ እንዲሆን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

ሠ. የተለያዩ የሳይበር ደህንነት መፍትሄዎችን ስራ ላይ ያውላል፤ እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ ስራ ላይ ለሚገኙ ሁሉም የመረጃ መሰረተ ልማቶች የሳይበር ደህንነት ድጋፍ ይሰጣል፤

ረ. ለተቋሙ በጣም ቁልፍ እና ሚስጥራዊ በሆኑ መረጃዎች ላይ መተግበር ስላለባቸው የሳይበር ደህንነት መሳሪዎች እና ዲዛይኖች ማለትም የጥቃት መከላከል ዘዴዎችን፣ የጥቃት ማስወገድ ዘዴዎችን፣ የመረጃ መጥፋት መከላከያ ዘዴዎችን፣ ፋየርዎል ወ.ዘ.ተ

ላይ የአዋጪነት ጥናት ያደርጋል፤ ለተግባራዊነታቸው ይሰራል፣ ያስተዳድራል፤

ሰ. የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ኢንጂነሪንግ ፕሮጀክት ያስተባብራል፤ ያስተዳድራል፤

ሸ. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን (ሶፍትዌርና ሃርድዌር) የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተቋሙን አውታረ-መረብ ደህንነት ይቆጣጠራል፤

ቀ. ተቋሙ በሚተገብራቸው ቁልፍ የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶች ላይ የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ደህንነታቸውን እንዲያረጋግጡ ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

በ. በሳይበር ደህንነት ስጋት ዳሰሳ መነሻ በማንኛውም የመቆጣጠሪያ ስርዓት ላይ አስፈላጊውን የደህንነት ቁጥጥር ስርዓት ይተገብራል፣ ያስተዳድራል፤

ተ. የሳይበር ደህንነትን ሊያዳብር የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅምን ይፈጥራል፤

ቸ. በአደጋ /ስጋት/ ዳሰሳ እና በጥልቀት የመከላከል መርህ መሰረት ወሳኝ የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂዎችን ስራ ላይ ያውላል፤

ኀ. የኮምፒውተሮችንና የአውታረ-መረቦችን ደህንነት ጠብቆ ይቀምራል (Configure)፣ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

ነ. የሳይበር ደህንነት ምርቶችንና አገልግሎቶችን ከሚያቀርቡ /ከሚሰጡ/ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት የተሳለጠ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ሂደቱን ይከታተላል፣ የእውቀት ሽግግርና የረጅም ጊዜ እደሳና ጥገና እንዲኖር ያደርጋል፤

ኘ. የሳይበር ደህንነት አስቸኳይ ሁኔታ ሲከሰት እና አደጋ ሲፈጠር የደህንነት ደረጃውን ከፍ ለማድረግ እቅዶችን እና ሂደቶችን ያለማል፤

አ. በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም ሲስተሞች ተደራሽነት የማግኘት ጥያቄዎችን በተቋሙ ፖሊሲ መሰረት ይቆጣጠራል፣ይፈቅዳል፤

ከ. የውስጥ ተጠቃሚዎችን የሲስተም አክሰስ እና ሲስተም ላይ የተሰሩ ስራዎችን ከሎግ በመነሳት ኦዲት ያደርጋል፤

2.7. የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና ግምገማ ቡድን (ክፍል)

አጭር መግለጫ

የተቋሙን የሥራ አውድ ባገናዘበ ሁኔታ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ የወጡ የሳይበር ደህንነት ስታንዳርዶችን መነሻ በማድረግ የሳይበር ደህንነት ኦዲት እና ምዘና ያከናውናል። በተቋሙ ውስጥ የተተገበሩ ቴክኖሎጂዎችን፣ የተቋሙን የሥራ ሂደት ደህንነት እና የደህንነት ተጋላጭነት በሚመለከት የተቀመጡ መስፈርቶችን፤ እንዲሁም ተቋሙ ሊከተላቸው በወሰናቸው እና በሚገደድባቸው ስታንዳርዶች መነሻ ኦዲት የማድረግ እና የደህንነት ፍተሻ/ምዘና/ በተከታታይነት ማድረግ፣ ለተገኙ ግኝቶችም የመፍትሄ መንገዶችን ይጠቁማል። በተጨማሪ የተቋሙ የሰው ሀይል የተቀመጡ የደህንነት መስፍርቶችን እየተከተለ መሆኑን ይገመግምል፤የደህንነት ንቃተ ህሊና ደርጃቸውን እየመዘነ ክፍተት ባገኘባቸው ቦታዎች የመፍትሄ ምክረ-ሃሳቦችን ያስቀምጣል። በተቋሙ ውስጥ የሚተገበሩ የቴክኖሎጂ ምርቶች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት የተቀመጡ የደህንነት መስፈርቶችን ማሟላት ወይም ያለመሟላታቸውን ፍተሻ ያከናውናል። በመሆኑም ዋና ዋና ተግባር እና ኃላፊነት ከታች የተገለጸ ሲሆን፣ የክፍኑ(የቡድኑ) የሥራ መደቦች ደግሞ በዚህ ሰነድ ክፍል ሁለት ተዘርዝሯል። በተያያዘም የሥራ ክፍሉ /ቡድን/ መሪ ሊኖሩት የሚገቡ የመወዳደሪያ አቅሞች /Competency/ ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 7) ተደርጓል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. በሀገር እና በአለም አቀፍ ደረጃ የወጡ መመዘኛዎች በመጠቀም ከሰዎች፣ ከቴክኖሎጂና ከሥራ ሂደቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችን ይለያል፤

ለ. ለሥርዓቱ ደህንነት ሲባል የተቀመጡ የደህንነት መስፈርቶችን ትግበራ ይፈትሻል፤

ሐ. የኢኮቴ ምርቶች ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት ተቋሙ ያስቀመጣቸውን የደህነነት መስፈርቶች እና የሚከተላቸውን ስታንዳርዶች የሚያሟሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የቅድመ ምዘና ስራ ያከናውናል።

መ. ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ የተቋሙን ውስጣዊ ተግባሮች ከተቀመጡ ገዢ ሰነዶች አንጻር እየተተገበሩ መሆንና አለመሆናቸውን ኦዲት ያደርጋል፤

ሠ. የተገኙ ክፍተቶችን በደረጃ በማስቀመጥ የመፍትሄ ሃሳቦችን ይጠቁማል፤

ረ. የሳይበር ደህንነት ኦዲት ግኝቶችን ለፕሬዝዳንት /ለዋና ዳሬክተር/ ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል፡፡

2.2. የሳይበር ደህንነት ክስተት ክትትል እና ምላሽ ቡድን (ክፍል)

አጭር መግለጫ

ይህ ቡድን (ክፍል) በተቋም ውስጥ የሳይበር ደህንነት ስጋት፣ ተጋላጭነትና ክስተት በፍጥነት እና በአስቸኳይ ለማስወገድ የሚያስችል የመከላከል ሥራ ይሰራል። የተቋሙ የሳይበር ደህንነት ጥቃት የመጀመሪያ ምላሽ ሰጪ አካል ነው። የሥራ ክፍሉ የሳይበር ጥቃቶችን/ችግሮችን/ ዋነኛ መንስኤ በማግኘት ጥቃቱ እንዳይፈጸም እና ዳግመኛ እንዳይከሰት በዋነኛነት ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ነው። ይህ ቡድን (ክፍል) የተቋሙን ወሳኝ የመረጃ ስርዓቶች፣ በይነ መረቦች፣ ድሮች እና ሚስጥራዊ ወይም የተከለከለ ውሂብ ጋር የተያያዘ ማንኛውም እውነተኛ ወይም የተጠረጠሩ ክስተቶች የሚከታተል እና ምላሽ የሚሰጥ፤ የተቋሙን የሳይበር ደህንነት ከውስጥ እና ከውጭ ከሚመጣ ክስተትና ጥቃት ይከላከላል። የሥራ ክፍሉ በመስኩ ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር የሚያደርግ፣ መስተጋብር ያለው፣ አውዳዊ፣ ተቋማዊ፣ ሀገራዊ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን ማጤን የግድ የሚለው፣ ስትራቴጂን መሰረት ያደረገ እና ተቋማዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ነው። በመሆኑም ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች ከታች የተገለጹ ሲሆን፣ የክፍሉ (ቡድኑ) የሥራ መደቦች ደግሞ በዚህ ሰነድ ክፍል ሶስት ተዘርዝረዋል። እንዲሁም የሥራ ቡድኑ(ክፍሉ) መሪ ሊኖሩት የሚገቡ የመወዳደሪያ አቅሞች /Competency/ ከዚህ ሰነድ ጋር አባሪ (ቅጽ 8) ተደርጓል።

ዋና ዋና ተግባሮች እና ኃላፊነቶች

ሀ. የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችን ያስተዳድራል፤ የተጋላጭነት ክፍተት የመለያ ስትራቴጂዎችን እና አሰራሮችን ያዘጋጃል፣ይተገብራል፤

ለ. የሳይበር ደህንነት ክስተት ቁጥጥር፣ ክትትል እና ምላሽ ስርዓት ይተገብራል፤

ሐ. የተቋሙን የኢንፎርሜሽን ስርዓት ክስተት ደህንነት ይከታተላል፤

መ. የተለያዩ የደህንነት መከላከያ ስርዓቶችን ያቅዳል፣ ይተገብራል፣ያሻሽላል፣ለጥቅም ያውላል፤

ሠ. የሳይበር ደህንነት ክስተት፣ ተጋላጭነትና አደጋ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

ረ. በተለያዩ የተቋሙ የስራ ክፍሎች ውስጥ ሊደርሱ የሚችሉ ክስተቶች ወይም የደህንነት ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ አጠራጣሪ ሁኔታዎችን በመለየት ተገቢው የመከላከል እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያሳውቃል፤

ሰ. ስርአቶች እና አውታረ-መረቦች በሰርጎ-ገቦች እንዳይጠቁ በንቃት ይቆጣጠራል፤

ሸ. ለሳይበር ደህንነት ችግር የመፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል አሰራሮችን ማዘጋጀት፤

ቀ. በሳይበር ደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ የትብብር እና የቅንጅት ግንኙነት ይፈጥራል፤

በ. ለሶስተኛ ወገን ክፍት የሚሆኑ ሲስተሞች ላይ ክትትል ያደርጋል፤የተጋላጭነት ሁኔታ ይከታተላል፤

ተ. የሳይበር ደህንነት ጥሰቶችን (security breaches) ዋነኛ ምክንያት ለማወቅ ትንታኔ ይሰራል፤ የተቋሙን ማህበረሰብ ያነቃል (Alert warning) ፤

ቸ. አግባብ የሆኑ የደህንነት መሳሪያዎችን ይጭናል (Installation)፤ የጥንቃቄ እርምጃዎችን አስመልክቶ ምክር ይሰጣል (recommendation) ፤

ኀ. የሳይበር ደህንነት ላይ ያልተለመዱና አጠራጣሪ ሁኔታዎችን በመለየት ችግሮችን ያሳውቃል፤ የአሰራርና ደንብ ጥሰት ሲያጋጥም ለሚመለከተው አካል ያመለክታል፤ ሪፖርት ያደርጋል፤

ነ. የተቋሙን ተጋላጭነት በተገቢ ሁኔታ ያስተዳድራል፤ የተጋላጭነት አያያዝ ስትራቴጂዎችን እና ሂደቶችን ያዘጋጃል፤ ያመቻቻል፤

ኘ. አስፈላጊ የሆኑ የጥበቃ የደህንነት ቴክኖሎጂዎችን የሚመለከቱ ወንጀሎች በወቅቱ ለትክክለኛዎቹ አካላት ሪፖርት ያደርጋል፤

አ. ከተለያዩ የተቋሙ ክፍሎች የሳይበር ጥበቃ ክስተቶችን እና አጠራጣሪ ክስተቶችን ለይቶ ያውቃል፤ ለእነዚህ ክፍሎች የቁጥጥር መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤

ከ. የሥራ ክፍሉን ሪፖርት በወቅቱ ለሚመለከተው አካላት ያቀርባል፤

ክፍል ሶስት፡ የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት የሥራ መደቦች

የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት ወደ ታችኛው እርከን ለማውረድ እና ለመተግበር ያመች ዘንድ ከላይ በክፍል ሁለት የተዘረዘሩትን አደረጃጀቶች ወይም የሥራ ክፍሎች (ቡድኖች) መነሻ በማድረግ ለእያንዳንዱ የሥራ ክፍሎች የሥራ መደብ መጠሪያ እና ደረጃ ተሰጥቷል። እንዲሁም በስምንት(8) ደረጃዎች በመዘርዘር ለእያንዳንዱ የሥራ መደቦች ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት፣ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ የሥራ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ እና ሰርተፍኬሽኖች፤ በተጨማሪ በሥራ መደቦቹ የሚመደቡ ባለሙያዎች ሊኖራቸው የሚገባ የመወዳደሪያ አቅም (Competency) በግልጽ በማስቀመጥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

3.1. የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ቡድን (ክፍል) የሥራ መደቦች

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: I

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ የተሰጠውን ተልዕኮ በመረዳትና እንደመነሻ በመውሰድ ተግባራትን ያከናውናል፤ ➢ የተሰማራበትን ኢንዱስትሪ ወይም የስራ ዘርፍ በአግባቡ በመረዳት ተግባራትን ያከናውናል፤ ➢ አጠቃላይ የሚሰራበትን ስነ ምህዳር ባህሪያት ይተነትናል፤ ➢ ቡድንን መሰረት ያደረገ የስራ ግንኙነት ይመሰርታል፤ ➢ ሰዎች የሚናገሩትን በአግባቡ ያዳምጣል፤ መልእክቱንም ወደ ራስ ይተረጉማል፤ ➢ የራስን ስራ በተደራጀ መልኩ ያቅዳል፣ ርእታዊ በሆነ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ስራውን ይሰራል፤ ይከታተላል፤	➢ መሰረታዊ የአሰስመንት እውቀት፤ ➢ መሰረታዊ የኔትወርክ እውቀት፤ ➢ መሰረታዊ ፕሮግራሚንግ እውቀት፤ ➢ መሰረታዊ የሪፖርት አጻጻፍ እውቀት፤ ➢ መሰረታዊ የሴክዩሪቲ እውቀት፤ ➢ የተቋማዊ ተልእኮ እውቀት፤	➢ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማዊ ፖሊሲዎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ሂደቶችን፣ ሜትዶሎጆችን እና ቱሎችን የመገንዘብ ክህሎት፤ ➢ ያወቃቸው እውቀቶች ራሱን ለማልማት በአግባቡ የመጠቀም፤ ➢ ክስተቶችን በፍጥነት የመረዳት፤ ➢ የተለያዩ አማራጮች የመገንዘብ፣ የማስተናገድ፤ ➢ ቡድንን መሰረት ያደረገ የስራ ግንኙነት የመመስረት፤ ➢ የሚሰራውን ስራ ስነ-ምህዳር ባህሪያት የመማር፣	የመጀመሪያ ዲግሪ በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በኮምፒተር ሳይንስ፣ በኢንፎርሜሽን ማናጅመንት ሲስተምስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ፡	ከ 0-1 ዓመት	

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ የተለያዩ አማራጮችን መገንዘብ፣ ማስተናገድ፤ እንዲሁም የሌሎች አስተዋፅኦ ጠቃሚ መሆኑ መገንዘብ፤ ➢ ቡድን መሰረት ያደረገ የስራ ግንኙነት መመስረት መቻል፤ ➢ ለሥራ-ዘርፉ የሚሆን እውቀት አጋዥ የሆኑ አካላት መለየት እና አስፈላጊውን እውቀት መጠቀም መቻል፤ ➢ ሰዎች ያሉትን በአግባቡ በማዳመጥ መልእክቱን በአግባቡ ወደ ራስ መተርጎም መቻል፤
➢ የሥራ ክባቢ የመገንዘብ ብቃት፤	➢ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ስራዎች አውዳዊነት ወይም ተጣጣሚነትን ለማረጋገጥ የተቋሙን ራዕይ፣ ተልእኮ፣ መዋቅር፣ ግቦች፣ አላማዎች፣ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚካዊ፣ ማህበራዊና ህጋዊ ፍላጎቶች የመረዳት፤ ➢ የስራ ባህል፣ ፍልስፍና፣ ተቋማዊ የስራ-ሂደቶች፣ ሃገራዊና አለም-አቀፋዊ ትስስርን፣ አለም አቀፍ ቴክኖሎጂካዊ አዝማሚያዎች እና ሌሎች አውዳዊ ጉዳዮች የመገንዘብ ብቃት፤
➢ መረጃ የመሰብሰብ ብቃት፤	➢ በቅርበትና በርቀት በሚገኝ የመረጃ ስርዓት ላይ ያሉ ተጋላጭነቶችን ለመለየት የሚረዱ የተለያዩ መረጃዎችን (ምሳሌ ኦፕሬቲንግ ሲስተም፣ ሰርቪስ፣ የተከፈቱ ፖርቶች፣ ወዘተ) የመሰብሰብ ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ፡ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ፡ II

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ የተሰማራበት ኢንደስትሪ ወይም የስራ ዘርፍ በመገንዘብ ተግባራትን ያከናውናል፤ ➢ የበላይ አካላት /የማናጅመንት/ ይሁንታን ለማግኘት የሚያስችል የግንኙነት እና የተግባቦት አቅም ይገነባል፤ ➢ ጠንካራ የሆነ የቡድን የስራ ግንኙነት ይመሰርታል፤ ➢ በሲስተም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ይለያል፤ ይተነትናል፤ ➢ ተግባራትን ከጥቅል ተልእኮ ጋር የማስተሳሰር ሥራ በጀማሪ ደረጃ ያከናውናል፤ ➢ የተለያዩ አማራጮችና የሌሎች አስተዋፅኦ ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ ያስተናግዳል፤ ➢ ለስራ ዘርፉ የሚሆን እውቀት አጋዥ የሆኑ አካላትን በመለየት አስፈላጊውን እውቀት ያሰባስባል፤ ➢ ከሱ ደረጃ በታች ያሉ አባላትን ያሰለጥናል፤ ያበቃል፤	➢ የሳይበር ደህንነት ክፍተቶች፣ ስጋቶች፣ የስጋት ምንጮች፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቭ (ፍላጎት)፣ የስጋት አይነቶች ግንዛቤ፤ ➢ የሚሰራበት ስነ-ምህዳር እውቀት፤ ➢ የኔትዎርክ ሴክዩሪቲ፤ ➢ የፊዚካል ሴክዩሪቲ፤ ➢ የኢንሲደንት ማናጅመንት፤ ➢ የሪፖርት አጻጻፍ፤ ➢ ሰነድ የመሰነድ፤	➢ የሚሰራበትን ስነ-ምህዳር ባህሪያት የመማር፣ እውቀት የማደራጀትና የማስተሳሰር፤ ➢ በተሰጠው ጉዳይ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የደህንነት ክፍተቶች፣ ስጋቶች፣ የስጋት ምንጮች፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቭ (ፍላጎት)፣ የስጋት አይነቶች የመለየት፣ የመተንተን እና የማደራጀት፤ ➢ የሚያደርሱ ተፅዕኖዎችን ተቋማዊ የሪስክ አሰስመንት (ስጋት ዳሰሳ) መርሆችና ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ የመለየት፣ የመተንተን እና የማደራጀት፤ ➢ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማዊ ፖሊሲዎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ሂደቶችን፣ ሜትዶሎጀዎችን እና ቱሎችን ፅንሰ-ሃሳብ የመገንዘብ፤ ➢ ሰዎችን በአግባቡ የማዳመጥ እንዲሁም መልእክቱን በአግባቡ ወደራስ የመተርጎም፤	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ ኮምፒተር ሳይንስ፣ በኢንፎርሜሽን ማናጅመንት ሲስተምስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ፤	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ1-2 ዓመት፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ0-1 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፤	

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ የተለያዩ አማራጮችን መገንዘብ፣ ማስተናገድ፤ እንዲሁም የሌሎች አስተዋፅኦ ጠቃሚ መሆኑ መገንዘብ፤ ➢ ቡድን መሰረት ያደረገ የስራ ግንኙነት መመስረት መቻል፤ ➢ ለሥራ-ዘርፉ የሚሆን እውቀት አ.ጎ የሆኑ አካላት መለየት እና አስፈላጊውን እውቀት መጠቀም መቻል፤ ➢ በአግባቡ የማዳመጥ እንዲሁም መልእክቱን በአግባቡ ወደ ራስ መተርጎም መቻል፤
➢ የስራ ክባቢ የመገንዘብ ብቃት	➢ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ስራዎች አውዳዊነት ወይም ተጣጣሚነትን ለማረጋገጥ የተቋሙን ራዕይ፣ ተልእኮ፣ መዋቅር፣ ግቦች፣ አላማዎች፣ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ህጋዊ ፍላጎቶችን መረዳት፣ ➢ የስራ ባህል፣ ፍልስፍና፣ ተቋማዊ የስራ-ሂደቶች፣ ሃገራዊና አለም-አቀፋዊ ትስስርን፣ አለም አቀፍ ቴክኖሎጂያዊ አዝማሚያዎች እና ሌሎች አውዳዊ ጉዳዮች የመገንዘብ ብቃት፤
➢ መረጃ የመሰብሰብ ብቃት	➢ በቅርበትና በርቀት በሚገኙ የመረጃ ስርዓት ላይ ያሉ ተጋላጭነቶችን ለመለየት የሚረዱ የተለያዩ መረጃዎችን (ምሳሌ አፕሬቲንግ ሲስተም፣ ሰርቪስ፣ የተከፈቱ ፖርቶች፣ ወዘተ) የመሰብሰብ ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: III

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ በሲስተም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነቶችን (risks) ይለያል፣ ይተነትናል፣ ➢ ስርአቶችን (ስታንዳርዶችን፣ ጋይድላይኖችን፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎችን እና ሌሎች ፍሬም ዎርኮችን) ከስተማይዝ ያደርጋል፣ ➢ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማዊ ፖሊሲዎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ሂደቶችን፣ ሜትዶሎጂዎችን እና ቱሎችን ፅንሰ-ሃሰብ ሙሉ በሙሉ ይገነዘባል፣ ➢ የደህንነት ክፍተቶችን፣ ስጋቶችን፣ የስጋት ምንጮችን፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቮችን፣ የስጋት አይነቶችን ይተነትናል፣ ይገመግማል፣ ያደራጃል፣ ➢ በተሰጠው ተግባር ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ/ያጋጠሙ ሪስኮች ወይም ጥቃቶች በጉዳዩ ላይ የሚያደርሱትን ተፅዕኖዎች ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ➢ በሥራ ክፍሎች መካከል ቀጣይና ውጤታማ የሆነ የስራ ግንኙነት ይመሰርታል፣	➢ በሰው ሃይል፣ በስራ ሂደት እና በኢኮቴ መሰረተ-ልማት ላይ የሚኖሩ ክፍተቶች፣ ስጋቶች እና ሪስኮች ዕውቀት፣ ➢ የተቋማዊ ተልዕኮ ዕውቀት፣ ➢ የኢንሲደንት ማናጅመንት ዕውቀት፣ ➢ የአፕሊኬሽን ሴክዩሪቲ ዕውቀት፣ ➢ የኔትዎርክ ሴክዩሪቲ ዕውቀት፣ ➢ የፊዚካል ሴክዩሪቲ ዕውቀት፣ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት አላማዎች፣ መርሆች፣ ግቦች፣ መዋቅር፣ ራእይ እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎች፣	➢ በተሰጠው ጉዳይ ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የደህንነት ክፍተቶችን፣ ስጋቶችን፣ የስጋት ምንጮችን፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቭ(ፍላጎት)፣ የስጋት አይነቶችን የመለየት፣ የመገምገም፣ የማደራጀት ➢ የሚያደርሱትን ተጽዕኖዎች ተቋማዊና ሃገራዊ የሪስክ አሰስመንት መርሆችና ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ የመለየት፣ የመገምገም፣ የማደራጀት፣ ➢ ለክፍሉ ውጤታማነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ፍሬምዎርኮችን የማዘጋጀት ክህሎት፣ ➢ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማዊ ፖሊሲዎች፣ ስታንዳርዶች፣ ሂደቶች፣ ሜትዶሎጆች እና ቱሎች ፅንሰ-ሃሰብ ሙሉ በሙሉ የመገንዘብ ክህሎት፣ ➢ ሰዎች ያሉትን በአግባቡ የማዳመጥ እንዲሁም መልእክቱን በአግባቡ ወደራስ የመተርጎም ክህሎት፣ ➢ የኢንፎርሜሽን ሴክዩሪቲ ሪስክ	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በኮምፒተር ሳይንስ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ፣	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ3-4 ዓመት፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ1-2 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፣	➢ Comp Security+ (ቢኖር ይመረጣል)

➢ ከደረጃው በታች ያሉ አባላትን ያሰለጥናል፤ ያበቃል፤		መፍትሄ ስታንዳርዶችን መሰረት በማድረግ መምረጥና ማቀናጀት፤ ➢ የተመረጡ መፍትሄዎችንና ፋይዳቸው የማስተሳሰር ክህሎት፤			

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ የተለያዩ አማራጮችን መገንዘብ፣ ማስተናገድ፤ እንዲሁም የሌሎች አስተዋፅኦ ጠቃሚ መሆኑ መገንዘብ፤ ➢ ቡድን መሰረት ያደረገ የስራ ግንኙነት መመስረት መቻል፤ ➢ ለሥራ-ዘርፉ የሚሆን እውቀት አጋዥ የሆኑ አካላት መለየት እና አስፈላጊውን እውቀት መጠቀም መቻል፤ ➢ ሰዎች ያሉትን በአግባቡ ማዳመጥ እንዲሁም መልእክቱን በአግባቡ ወደ ራስ መተርጎም መቻል፤
➢ የስራ ከባቢ የመገንዘብ ብቃት፤	➢ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ስራዎች አውዳዊነት ወይም ተጣጣሚነትን ለማረጋገጥ የተቋሙን ራዕይ፣ ተልእኮ፣ ግቦች፣ አላማዎች፣ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ህጋዊ ፍላጎቶችን የመረዳት፤ ➢ የስራ ባህል፣ ፍልስፍና፣ ተቋማዊ የስራ-ሂደቶች፣ ሃገራዊና አለም-አቀፋዊ ትስስርን፣ አለም አቀፍ ቴክኖሎጂያዊ አዝማሚያዎች እና ሌሎች አውዳዊ ጉዳዮች የመገንዘብ ብቃት፤
➢ መረጃ የመሰብሰብ ብቃት፤	➢ በቅርበትና በርቀት በሚገኙ የመረጃ ስርዓት ላይ ያሉ ተጋላጭነቶችን ለመለየት የሚረዱ የተለያዩ መረጃዎችን (ምሳሌ ኦፕሬቲንግ ሲስተም፣ ሰርቪስ፣ የተከፈቱ ፖርቶች፣ ወዘተ) የመሰብሰብ ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: IV

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ ከፕሮጀክት በታች የሚታዩ ቡድኖችን ያስተባብራል፤ ለቲሙ ቴክኒካል አስተዋጽኦ ያበረክታል፤ ➢ ከደረጃ IV በታች ያሉ አባላትን ያስለጥናል፤ ያበቃል፤ ➢ በስራ ሂደቱ ላይ የሚኖሩ ባለድርሻ አካላትን ይተነትናል፤ ➢ የበላይ አካላትን ይሁንታ ለማግኘት የሚያስችል የግንኙነት እና የተግባቦት አቅም ይፈጥራል፤ ➢ በሲስተም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ክስተቶች የመለየትና የመተንተን ስርአቶችን (ስታንዳርዶች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ያበለጽጋል፤ ያሻሽላል፤ ➢ ተቋማዊ ፍላጎትን፣ ራእይን፣ አላማን፣ መርሆችን፣ ግቦችን፣ እና	➢ የተቋማዊ ተልእኮ ዕውቀት፤ ➢ የደህንነት ክፍተቶች፣ ስጋቶች፣ የስጋት ምንጮች፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቮች፣ የስጋት አይነቶች ግንዛቤ፤ ➢ የኢንሲደንት ማናጅመንት ዕውቀት፤ ➢ የአፕሊኬሽን ሴክዩሪቲ፤ ➢ የኔትዎርክ ሴክዩሪቲ፤ ➢ የፊዚካል ሴክዩሪቲ፤ ➢ የሪስክ አሰሳመንት ሜትዶሎጂዎች ወይም ቱሎች፤ ➢ የስጋት ዳሰሳ ጥናትና ትንተና፤ ➢ የሪስክ ማኔጅመንት፤	➢ ተቋማዊ የስራ ሂደቶች ላይ የሚኖሩ ባለድርሻ አካላት የትንተና ክህሎት፤ ➢ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማዊ የፖሊሲዎች፣ የስታንዳርዶች፣ የሂደቶች፣ የሜትዶሎጆዎች እና የቱሎች ፅንሰ-ሃሳብ ሙሉ በሙሉ የመገንዘብ ክህሎት፤ ➢ የሚሰራውን ስራ ስነ-ምህዳር ባህሪያት የመማር፣ የማደራጀት እና የማስተሳሰር ክህሎት፤ ➢ ተግባራትን ከጥቅል ተልእኮ ጋር የማስተሳሰር ክህሎት፤ ➢ ቀጣይና ውጤታማ የሆነ ኢንተር-ዲፓርትመንታል የስራ ግንኙነት የመመስረት ክህሎት፤ ➢ የፕሮጀክት አባላትን የማስተባበር፣ ክህሎት፤ ➢ የተለያዩ አማራጮችን የመገንዘብ ክህሎት፤ ➢ ሰዎች የሚናገሩትን በአግባቡ የማዳመጥ እንዲሁም መልእክቱን በአግባቡ ወደራስ የመተርጎም ክህሎት፤ ➢ ውሳኔ የመስጠት ክህሎት፤ ➢ ለክፍሉ ውጤታማነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ፍሬምዎርኮችን ማዘጋጀት	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በኮምፒተር ሳይንስ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ፡	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ4-5 ዓመት፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ2-3 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፤	➢ ISO 27001 lead implementer ወይም ➢ Comp Security+ (ቢኖር ይመረጣል)

ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት ትስስራቸውን በመገንዘብ ይተነትናል፤ ያደራጃል፤ ➢ ወጪ ቆጣቢና ምርጥ የኢንፎርሜሽን ሴኩሪቲ መፍትሄዎችን ይመርጣል፤ ይተነትናል፤ ያደራጃል፤		መቻል፤ ➢ ተቋማዊ የሴክዩሪቲ ፍላጎት፣ አላማ፣ መርሆች፣ ግቦች፣ ራእይ እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት መገንዘብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት እና ትስስራቸውን የመገንዘብና የማደራጀት ክህሎት፤			

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ በሥራ ክፍሎች መካከል ቀጣይና ውጤታማ የሆነ የስራ ግንኙነት መመስረት፤ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ማዕቀፎች ዝግጅት ፕሮጀክቶችን መምራት፤ ➢ የበላይ አካላት/ማኔጅመንት/ ይሁንታ ለማግኘት የሚያስችል የግንኙነት እና የተግባቦት አቅም፤
➢ የድራፍቲንግ/የመሰነድ/ ብቃት፤	➢ በሲስተም ደረጃ እና በተቋም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶች (ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ፅንሰ-ሃሳቦችን እና ፍላጎቶችን ማብላላት፣ ቅጥ ማስያዝ፣ መግለፅ፣ ማያያዝ፣ ማደራጀት እና መሰነድ፤
➢ የመተንተን ብቃት፤	➢ ተቋማዊ የደህንነት ክስተቶች መፍትሄ አቅጣጫ ጭብጥ ሞዴል በቂ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ህጋዊ ፋይዳ ያላቸው መስተጋብር እና ችግር ፈቺነታቸውን ትንተና ማድረግ፤
➢ የተፅእኖ ፈጣሪነት ብቃት፤	➢ ተቋም ተኮር የሆኑ የሳይበር ደህንነት ፍሬምዎርኮች በተቋሙ ተቀባይነት እንዲያገኙ ማሳመን፣ መግባባት መፍጠር፤ ➢ በተቋም ደረጃ የተዘጋጁ የሳይበር ደህንነት ፍሬምዎርኮች ምን ያክል ፋይዳ እንዳላቸው ፍንትው አድርጎ ማሳየት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: V

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ ተቋማዊ የሴክዩሪቲ ፍላጎት፣ ራእይ፣ አላማ፣መርሆች፣ግቦች፣መዋቅር፣ እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያስተሳስራል፤ ➢ በሲስተም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማናጅመንት ስርአቶች (ስታንዳርዶች፣ ጋይድላይኖች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ያበለጽጋል፤ ያሻሽላል፤ ➢ ተቋማዊ የስራ ሂደቶች ላይ የሚኖሩ ባለድርሻ አካላት ተግባር ይተነትናል፤ ➢ ተቋማዊ ግንኙነት ወይም ትስስር መፍጠር የሚያስችሉ ሂደቶችን ይቀርጻል፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ከተቋማዊ ተልዕኮ፣ ፍላጎት፣ ፍልስፍና፣ እሴት እና የስራ ባህል ያላቸውን ትስስር ይተነትናል፤ ➢ ማዕቀፎች ፣ ሞዴሎች እና አርክቴክቸሮችን ይነድፋል፤ ➢ ለማናጀሮች እና ለስራ አስፈፃሚዎች ሰፊ ስትራተጂክ ምክር ይሰጣል፤ ➢ ፕሮጀክት ይመራል፤	➢ ተቋማዊ የሴክዩሪቲ ፍላጎት፣ራዕይ፣ አላማ፣ መርሆች፣ ግቦች፣ መዋቅር እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎች፤ ➢ የደህንነት ክፍተቶች፣ ስጋቶች፣ የስጋት ምንጮች፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቮች፣ የስጋት አይነቶች የላቀ እውቀት፤ ➢ አካላዊ/ቁሳዊ/፣ ከባቢያዊ፣ ቴክኒካዊ፣ ሂደቶች እና ሰውን መሰረት ያደረጉ የሳይበር ደህንነት መቆጣጠሪያዎች ዕውቀት፤ ➢ ኢንተርናሽናል የሳይበር ደህንነት ስታንዳርዶች፣ ሞዴሎች፣ አርክተክቸሮች፣ ሜትዶሎጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች፤ ➢ ኢንፍራስትራክቸር ሴክዩሪቲ ዕውቀት፤	➢ ተቋማዊ የሴክዩሪቲ ፍላጎትን፣ ራዕይ፣ አላማ፣ መርሆች፣ግቦች፣መዋቅር እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት መገንዘብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት እና ትስስራቸውን የመገንዘብና የማደራጀት ክህሎት፤ ➢ የስራ ሂደቶች ትስስርን በአግባቡ የመለየት፣ የመገንዘብ፣ የመተንተንና የማደራጀት ክህሎት፤ ➢ የባለድርሻ አካላት ትንተና ማድረግ፤ ➢ ወጪ ቆጣቢና ምርጥ የኢንፎርሜሽን ሴኩሪቲ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የመምረጥ፣ የመገምገምና የማቀናጀት ክህሎት፤ ➢ ተቋማዊ ቅንጅት ወይም ትስስር የመፍጠር ክህሎት፤ ➢ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የግንኙነት ክህሎት፤	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ ፣ በኮምፒተር ሳይንስ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ፡	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ5-6 ዓመት፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ3-4 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፤	➢ CEH ወይም ➢ ISO 27001 lead implementer ወይም ➢ project management ወይም ➢ risk management (ቢኖር ይመረጣል)

➢ የስራ ሂደት ይቀርጻል፤ ይተገብራል፤ ➢ ከደረጃው በታች ያሉ አባላትን ያሰለጥናል፤ ያበቃል፤ ➢ የተለያዩ የስራ ሂደቶችን ትስስር/ተመጋጋቢነት/ በአግባቡ ይለያል፣ ይገነዘባል፣ ይተነትናል፤ ያደራጃል፤ ➢ ፈጠራና ግኝት በተሞላበት አኳሃን መፍትሄዎች ያመጣል፤ ➢ ተግባራዊ የተደረጉ የሳይበር ደህንነት መቆጣጠሪያዎችን ውጤታማነት ይተነትናል፤ ➢ ቁልፍ እና ከፍተኛ ደረጃ ካላቸው ባላድርሻ አካላት ጋር አብሮ ይሰራል፤		➢ የተመረጡ መፍትሄዎችና ፋይዳቸውን የማስተሳሰር ክህሎት፤ ➢ በስራ ዘርፎች የተለዩ ፅንሰ-ሃሳቦችን እና የሴክዩሪቲ ፍላጎቶችን ማብላላት፣ ቅጥ የማስያዝ፣ የማስተሳሰር፣ የማደራጀ እና የመሰነድ ክህሎት፤ ➢ ተቋማዊ ቁልፍ ጉዳዮች እና ሀብቶች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የደህንነት ክፍተቶች፣ ስጋቶች፣ የስጋት ምንጮች፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቮች፣ የስጋት አይነቶች የሪሰክ አሰስመንት መርሆችንና ፍላጎቶችን መሰረት በማድረግ የመለየት፣ የመገምገም፣ የማደራጀት፤ ➢ በተቋማዊ ተልዕኮ ቁልፍ ጉዳዮች እና ሀብቶች ላይ ያጋጠሙ/ ሊያጋጥሙ/ የሚችሉትን የሴክዩሪቲ ክስተቶች ተቋሙ እና ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ			

		የመተንተን፣ የመገምገም፣ የማደራጀት፤			

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ ድራፍቲንግ/ የመሰነድ/ ብቃት፤	➢ በተቋም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶች (ስታንዳርዶች፣ ጋይድላይኖች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ፅንሰ-ሃሳቦችን እና ፍላጎቶችን ማብላላት፣ቅጥ ማስያዝ፣ መግለፅ፣ ማያያዝ፣ ማደራጀት እና መሰነድ፤
➢ የመተንተን ብቃት፤	➢ ተቋማዊ የሴክዩሪቲ ክስተቶች መፍትሄ አቅጣጫ ጭብጥ ሞዴል በቂ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ህጋዊ ፋይዳ ያላቸው መስተጋብር እና ችግር ፈቺነታቸውን ትንተና ማድረግ፤
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ በሥራ ክፍሎች መካከል ቀጣይና ውጤታማ የሆነ የስራ ግንኙነት መመስረት፤ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ማዕቀፎች ዝግጅት ፕሮጀክቶችን መምራት፤ ➢ የበላይ አካላት/ማኔጅመንት/ ይሁንታ ለማግኘት የሚያስችል የግንኙነት እና የተግባቦት አቅም፤
➢ የተፅእኖ ፈጣሪነት ብቃት፤	➢ ተቋም ተኮር የሆኑ የሳይበር ደህንነት ፍሬምዎርኮች በተቋሙ ተቀባይነት እንዲያገኙ ማሳመን፣ መግባባት መፍጠር፤ ➢ በተቋም ደረጃ የተዘጋጁ የሳይበር ደህንነት ፍሬምዎርኮች ምን ያክል ፋይዳ እንዳላቸው ፍንትው አድርጎ ማሳየት፤
➢ የመፍጠርና የማሻሻል ብቃት፤	➢ በሲስተም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶች (ስታንዳርዶች፣ መመሪያዎች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ማበልፀግ፣ ማሻሻል፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: VI

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ በተቋም ደረጃ ተፅእኖ ያላቸው የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት መርሆች፣ ሞዴሎች፣ ሜትዶሎጂዎች፣ የስራ ሂደቶች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች ይቀምራል፣ ያበለጽጋል፤ እንዲሁም ለተቀባይነታቸውና ተግባራዊነታቸው ተፅእኖ ይፈጥራል፤ ➢ ሃገራዊ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ህጋዊ ፍላጎቶች፣ መርሆች፣ ፍልስፍናዎች እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት ይገነዘባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ያስተሳስራል፤ ➢ የስራ አከባቢው ባለድርሻ አካላትን ይለያል፤ ይተነትናል፤ ተጣጣሚነትን ያረጋግጣል፤ ➢ በመስኩ ሃገራዊ ቅንጅት እንዲመጣ ይሰራል፤ ➢ ፈጠራና ግኝት በተሞላበት አካኋን መፍትሄዎችን ያመጣል፤ ➢ ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶችን ይመራል፤	➢ የሳይበር ደህንነት ገቨርናንስ ፅውቀት፤ ➢ የተቋማዊ ባህልና ባህሪ (የስራ-ሂደት፣ ስራ-ሂደት ዘርፍ፣ መዋቅር፣ የስራ ባህል፣ አስተሳሰብ፣ ተልእኮ፣ ራዕይ፣ግብ፣ አላማ ወዘተ) ፅውቀት፤ ➢ የፕሮግራም፣ የፕሮጀክት የማናጅመንት ፅውቀት፤ ➢ የቢዝነስ ስትራተጂ ፅንሰ ሃሰቦች እውቀት፤ ➢ የባለ ድርሻ አካላት እና የሶስተኛ ወገን ማኔጅመንት ፅውቀት፤	➢ ሃገራዊ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ህጋዊ ፍላጎቶች፣ መርሆች፣ ፍልስፍናዎች እና ሌሎች አውዳዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት የመገንዘብ፣ የመተንተን፣ የማደራጀት እና የማስተሳሰር ክህሎት፤ ➢ ባለድርሻ አካላትን የመለየት እና የመተንተን ክህሎት፤ ➢ መፍትሄ ከችግሮች ፈልቅቆ የማውጣት ክህሎት፤ ➢ የማሳመን ክህሎት፤ ➢ በዘርፎች የተለዩ ፅንሰ-ሃሳቦችን እና የሴኩሪቲ ፍላጎቶችን የማብላላት፣ ቅጥ የማስያዝ፣ የማስተሳሰር፣ የማደራጀት እና የመሰነድ ክህሎት፤ ➢ ተቋማዊ ቁልፍ መሰረተ-ልማቶች ላይ የሚደረገውን የኢንፎርሜሽን ሪስክ አሰስመንት ፕሮግራም የማቀድ፣የመምራት፣ የመገምገም ክህሎት፤ ➢ በተቋማዊ ተልዕኮና ወሳኝ ሀብቶች ላይ የሚደረገውን የኢንፎርሜሽን ሪስክ ትንተና ፕሮግራም የማቀድ፣ የመምራት፣ የመገምገም፤	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣፣ በኮምፒተር ሳይንስ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ፡	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ6-7 ዓመት፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ4-5 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፣	➢ CEH ወይም ➢ CRISK ወይም ➢ ISO 27001 lead impleme nter ወይም ➢ Project manage ment ወይም ➢ Risk manage ment (ቢኖር ይመረጣል)

➢ ማዕቀፎች ፣ ሞዴሎች እና አርክቴክቸሮች ይነድፋል፤ ➢ ከደረጃው በታች ያሉ አባላትን ያሰለጥናል፤ ያበቃል፤ ➢ ሁሉን አቀፍ ተቋማዊ የደህንነት ክፍተቶች፣ ስጋቶች፣ የስጋት ምንጮች፣ የስጋት ኤጀንት ሞቲቮች፣ የስጋት አይነቶች ይለያል፣ ይገመግማል፤ ያደራጃል፤ ➢ ተቋማዊ ሪስክ ማናጅመንት ፕሮግራም ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቀምራል፤ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ሪስክ ሚቲጌሽን(የስጋት ማለዘቢያ) ስትራቴጂ ይነድፋል፤ ➢ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሪስኮች ለይቶ ያወጣል፤ ➢ በተሰማራበት ዘርፍ ስትራቴጂክ እቅድ ይቀርጻል፤ ይተገብራል፤ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ማናጅመንት ስራዎችን ይለካል፣ ይገመግማል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤		➢ ሃገራዊ ሪስክ ትንተና መሰረት በማድረግ ወጥና ምክኒያታዊ የሆነ ሁሉ አቀፍ የሪስክ መፍትሄ ስትራተጂ የመንደፍ ክህሎት፤ ➢ የፅንሰ-ሀሳቦች ፋይዳ፣ መስተጋብር፣ ችግር ፈቺነታቸው ትንተና የማድረግ ክህሎት፤ ➢ መሳኢ አዝማሚያዎች በጥልቀት የመገንዘብ፣ የመተንተን እና ወደራስ የማስተሳሰር ክህሎት፤ ➢ አብሮ የመስራት ክህሎት፤ ➢ ችግሮችን የመለየት ክህሎት፤ ➢ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የማስተሳሰር፣ ፋይዳቸውን የማስላት ክህሎት፣ ➢ ፍላጎቶችን የማብላላት፣ ቅጥ የማስያዝ፣ የማስተሳሰር፣ የማደራጀት እና የመሰነድ ክህሎት፤			

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ ድራፍቲንግ/ የመሰነድ/ ብቃት፤	➢ በሲስተም ደረጃ እና በተቋም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶች (ስታንዳርዶች፣መመሪያዎች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ፅንሰ-ሃሳቦችን እና ፍላጎቶችን ማብላላት፣ቅጥ ማስያዝ፣ መግለፅ፣ ማያያዝ፣ ማደራጀት እና መሰነድ፣
➢ የሙተንተን ብቃት፤	➢ ተቋማዊ የሴክዩሪቲ ክስተቶች መፍትሄ አቅጣጫ ጭብጥ ሞዴል በቂ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ህጋዊ ፋይዳ፣ ያላቸው መስተጋብር እና ችግር ፈቺነት ትንተና ማድረግ፣
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ በሥራ ክፍሎች መካከል ቀጣይና ውጤታማ የሆነ የስራ ግንኙነት መመስረት፣ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ማዕቀፎች ዝግጅት ፕሮጀክቶችን መምራት፣ ➢ የበላይ አካላት/ማኔጅመንት/ ይሁንታ ለማግኘት የሚያስችል የግንኙነት እና የተግባቦት አቅም፣
➢ የተፅእኖ ፈጣሪነት ብቃት፤	➢ ተቋም ተኮር የሆኑ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች በተቋሙ ተቀባይነት እንዲያገኙ ማሳመን፣ መግባባት መፍጠር፤ ➢ በተቋም ደረጃ የተዘጋጁ የሳይበር ደህንነት ፍሬምዎርኮች ምን ያክል ፋይዳ እንዳላቸው ፍንትው አድርጎ ማሳየት፤
➢ የመፍጠርና የማሻሻል ብቃት፤	➢ በሲስተም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶች (ስታንዳርዶች፣ጋይድላይኖች፣ ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ማበልፀግ፣ ማሻሻል፤
➢ ችግሮችንና መፍትሄዎችን የማስተሳሰር ብቃት፤	➢ በሲስተም ደረጃ የሚለዩት የሪስኮች የመፍትሄ አቅጣጫዎች የተቋሙን ፍላጎት፣ ነባራዊ ሁኔታን የሚመልሱና ሁሉ አቀፍ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ ➢ የተለዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎች የሚያስገኙትን ትክክለኛ ጥቅም ማስላት፤ ➢ የተለዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎች የጎንዮሽ ጉዳት እንዳይኖራቸው ማረጋገጥ፤ ➢ እያንዳንዱን ሪስክ መፍትሄ እንደተቀመጠላት ማረጋገጥ፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: VII

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ በሴክተር ደረጃ ተፅእኖ ያላቸው የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት መርሆችን፣ ሞዴሎችን፣ ሜትዶሎጂዎችን፣ የስራ ሂደቶችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሌሎች ማዕቀፎችን ይቀምራል፣ ያበለጽጋል፣ ተቀባይነታቸውን ይከታተላል፤ ➢ ሃገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ማናጅመንት ማዕቀፎች ብልፀጋ ፕሮጀክቶች ላይ ይሳተፋል፤ ➢ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሪስኮች የመፍትሄ አቅጣጫ ስትራቴጂን ለይቶ ያወጣል፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ፍላጎቶች ተጣጣሚነትን ያረጋግጣል፤ ➢ የተሰማራበትን ዘርፍ ስትራቴጂክ እቅድ ይቀርጻል ፣ ይተገብራል፤ ➢ የሃገራዊ ፍላጎቶችንና የተሰማራበትን ምህዳር ጥልቅ አረዳድና አዝማሚያዎች ያነባል፣ ይተነትናል፣ የአዝማሚያዎቹን ተጽእኖ	➢ የቢዝነስ ስትራቴጂ ፅንሰ- ሃሰቦች፤ ➢ የተቋማዊ አውዳዊ ኩነቶች ፖሊቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ ሁኔታዎች፤ ➢ የስትራቴጂ፣ የፖሊሲ ንድፍ፤ ➢ ተቋማዊ የሳይበር ደህንነት ስታንዳርዶች፣ ሜትዶሎጂዎች፣ ሞዴሎች፣ መመሪያዎች፣ ምርጥ ተሞክሮዎች እና ፍሬምዎርኮች፤ ➢ የስርአት ንድፈ-ሃሳብ፤ ➢ የሳይበር አስተዳደር፤ ➢ የቅንጅታዊ-ስርአት፤ ➢ የፕሮጀክት ማኔጅመንት እውቀት፤	➢ የሳይበር ደህንነት ፍሬምዎርክ ኮንሰፕት(ጭብጥ) ሞዴል የመቅረፅ/ የማዘጋጀት ክህሎት፤ ➢ መፃኢ አዝማሚያዎችን በጥልቀት የመገንዘብ፣ የመተንተን እና ወደ ራስ የማስተሳሰር ክህሎት፤ ➢ አብሮ የመስራት ክህሎት፤ ➢ ክፍለ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ቅንጅትን የመፍጠር ክህሎት፤ ➢ ችግሮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የማስተሳሰር፣ ፋይዳቸውን የማስላት ክህሎት፤ ➢ የማሳመንና የመደራደር ክህሎት፤ ➢ ፅንሰ-ሃሳቦችንና ፍላጎቶችን የማብላላት፣ ቅጥ የማስያዝ፣ የማስተሳሰር፣ የማደራጀት እና የመሰነድ ክህሎት፤ ➢ በሃገራዊ ወሳኝ ጉዳዮች እና ሀብቶች ላይ ያጋጠሙ/ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን የሴክዩሪቲ ክስተቶች በተቋም ወይም በሃገር ደረጃ የሚያደርሱትን ተፅእኖ የመተንተን፣ የመገምገም፣ የማደራጀት ክህሎት፤ ➢ ሃገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ተፅእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የሪስክ አሰስመንትና	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ ፣ በኮምፒተር ሳይንስ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ፡	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ7-8 ዓመት፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ5-6 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፤	➢ CISM ወይም ➢ CISSP ወይም ➢ CISO ወይም ➢ CEH ወይም ➢ CRISK ወይም ➢ ISO 27001 lead implementer ወይም ➢ ITIL ወይም ➢ Project management ወይም ➢ Risk management (ቢኖር ይመረጣል)

ይተነብያል፤ ➢ ከደረጃው በታች ያሉ አባላትን ያሰለጥናል፣ ያበቃል፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ሪስክ ማገገሚያ ስትራቴጂ ውጤት ይለካል፤ ➢ ሃገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ሪስክ ማናጅመንት ፕሮጀክቶችን ይመራል፤ ➢ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሪስኮችን ለይቶ ያወጣል፤ ➢ ተቋማዊ፣ ሃገራዊ እና አለም አቀፋዊ እይታዎችን ይተነትናል፤		ትንተና መርሆች፣ ሞዴሎች፣ ሜትዶች፣ ሂደቶች እና ሌሎች አዳዲስ ንድፈ-ሃሳቦችን የመቀመር፣ የማበልፀግ፤ ➢ ወጥና ምክንያታዊ የሆነ ሁሉን አቀፍ የሪስክ ትንተና ስትራቴጂ የመንደፍ፤ ➢ ሀሳቦችን የማያያዝ፣ የማደራጀት እና ቅጥ እንዲይዝ የማድረግ ክህሎት፤ ➢ መፃኢ አዝማሚያዎችን በጥልቀት የመገንዘብ፣ የመተንተን እና ወደ ራስ የማስተሳሰር ክህሎት፤			

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ የማስተባበርና የማቀናጀት ብቃት፤	➢ ተግባራት በሚገባ ሁኔታ እንዲከናወኑ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የማሟላት፣ የጊዜ ሰሌዳውን የመቅረፅ፣ ለሚመለከታቸው አካላት የማሳወቅ እና ስራው በተሳካ ሁኔታ እንዲሰራ ቀድሞ መሰራት ያለባቸውን ስራዎች በሚገባ የማስተባበርና የማቀናጀት ብቃት፣
➢ የመፍጠርና የማሻሻል ብቃት፤	➢ በተቋም ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ስርአቶችን (ጋይድላይኖች፣ሞዴሎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች) ማበልፀግ እና ማሻሻል፤
➢ ችግሮችንና መፍትሄዎችን የማስተሳሰር ብቃት፤	➢ በተቋም ደረጃ የሚለዩት ሪስኮችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች የተቋሙን ፍላጎት እና ነባራዊ ሁኔታን የሚመልሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ ➢ በተቋም ደረጃ የሚለዩት ሪስኮች፣ የሚቀመጡት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ሁሉን አቀፍ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ ➢ የተለዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎች የሚያስገኙትን ትክክለኛ ጥቅም ማስላት፤ ➢ የተለዩ መፍትሄዎች የጎንዮሽ ጉዳት እንዳይኖራቸው ማረጋገጥ፤ ➢ እያንዳንዷን ሪስክ የመፍትሄ አቅጣጫ እንደተቀመጠላት ማረጋገጥ፤
➢ የማማከር ብቃት፤	➢ የተቋሙን ከፍተኛ አመራሮች በሳይበር ደህንነት ዙሪያ ማማከር፤
➢ ጉዳዮችን በተለያዩ አቅጣጫዎች የማየት ብቃት፤	➢ የሳይበር ደህንነት ስርዓት ቀረጻ እና ትግበራ ላይ ከተለያየ አቅጣጫዎች (ከፖለቲካ፣ ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከህጋዊ፣ ወዘተ..) የማየትና ሁለንተናዊነትን በተላበሰ አኳሃን የመቃኘት፣ የመገንዘብ በኮምፒተንሲው ዙሪያም የማማከር ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ባለሙያ

ደረጃ: VIII

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	እውቀት	ክህሎት	የትምህርት ደረጃ	የሥራ ልምድ	ሰርተፍኬት
➢ በዘርፉ አለም-አቀፍ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ ሁኔዎችን ይተነብያል፣ ይተነትናል፤ ➢ የሳይበር ደህንነት የመፍትሄ አቅጣጫ ስትራቴጂ ኮንሰፕት ሞዴል ይቀርጻል፤ ➢ ሃገራዊ ወይም አለም አቀፍ ተፅእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት መርሆችን፣ ሞዴሎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ሜትዶሎጂዎችን፣ ስትራቴጆዎችን፣ የአሰራር-ሂደቶችን እና ሌሎች አዳዲስ ንድፈ-ሀሳቦችን ይቀምራል፣ ያበለጽጋል፤ ተቀባይነታቸውንና ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ሃገራዊና አለም-አቀፋዊ ተጣጣሚነትን ያረጋግጣል፤	➢ የሃገራዊ አውዳዊ ኩነቶች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ ሁኔታዎች፤ ➢ አለም-አቀፋዊ ሁኔታዎች (ከሳይበር ደህንነት ጋር ተያይዞ) ግንዛቤ፤ ➢ ፖሊሲና ስትራቴጂ የመንደፍ፤ ➢ አለም-አቀፋዊ ወይም ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ስታንዳርዶች፣ ሜትዶሎጂዎች፣ ሞዴሎች፣ መመሪያዎች፣ ምርጥ ተሞክሮዎች እና ሌሎች ፍሬምዎርኮች ዕውቀት፤ ➢ የውጤታማነት ቅንጅት ዕውቀት፤	➢ ወጥና ምክንያታዊ የሆነ ሁሉን አቀፍ የሳይበር ደህንነት የመፍትሄ አቅጣጫ ስትራቴጂ ኮንሰፕት ሞዴል የመቅረፅ ፤ ➢ ሃገራዊ ወይም አለም አቀፋዊ ተፅእኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት መርሆች፣ ሞዴሎች፣ ስታንዳርዶች፣ ፖሊሲዎች፣ ሜትዶሎጂዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የአሰራር-ሂደቶች፣ ጋይድላይኖች እና ሌሎች አዳዲስ ንድፈ-ሀሳቦችን የመቀመር፣ የማበልፀግ፤ ➢ ሁሉን አቀፍ የሪስክ መፍትሄ ስትራቴጂ ተፈፃሚነትን መለካት እንዲሁም ለተፈፃሚነቱ ተፅእኖ የመፍጠር ብቃት፤ ➢ በሃገራዊ ቁልፍ መሰረተ-ልማት ላይ የሚደረገውን የሳይበር ደህንነት ሪስክ ትንተና ፕሮግራም የማቀድ፣ የመምራት፣ የማቀናጀት፣	በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ ወይም በኮምፒተር ሳይንስ ወይም በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ወይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም የሁለተኛ ዲግሪ፤	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ8-9 ዓመት፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ6-7 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ፤	➢ CISM ወይም ➢ CISSP ወይም ➢ CISO ወይም ➢ CEH ወይም ➢ CRISK ወይም ➢ ISO 27001 lead implementer ወይም ➢ ITIL ወይም ➢ Project management ወይም ➢ Risk management (ቢኖር ይመረጣል)

		የመገምገም ብቃት፤ ➢ አጠቃላይ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ማናጅመንት ጉዳዮች ላይ መንግስትን የማማከር ክህሎት፤ ➢ መሳኢ አዝማሚያዎችን በጥልቀት የመገንዘብ፣ የመተንተን እና ወደ ራስ የማስተሳሰር ክህሎት፤			
➢ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ማኔጅመንት ጉዳዮች ላይ መንግስትን በማማከር ሂደት ድርሻ ያበረክታል፤ ➢ ጥናታዊ ፅሑፎችን ያዘጋጃል፤ ➢ በመስኩ አለም- አቀፋዊ ግንኙነትን ይፈጥራል፤ ➢ ተቋማዊ፣ አገራዊ እና አለም አቀፋዊ እይታዎችን ይቀርጻል፤ ➢ ሃገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ሪስክ ማናጅመንት ፕሮጀክቶችን ይመራል፤ ➢ ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ሪስኮች እንድምታቸውን ይተነትናል፤ ➢ የሃገራዊ ፍላጎቶችንና የተሰማራበትን ምህዳር ጥልቅ አረዳድ እና አዝማሚያዎች ያነባል፣ ይተነትናል፣ የአዝማሚያዎቹን ተጽእኖ ይተነብያል፤					

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ የማስተባበርና የማቀናበር ብቃት፤	➢ ተግባራት በሚገባ ሁኔታ እንዲከናወኑ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የማሟላት፣ የጊዜ ሰሌዳውን የመቅረፅ፣ ለሚመለከታቸው አካላት የማሳወቅ እና ስራው በተሳካ ሁኔታ እንዲሰራ ቀድሞ መሰራት ያለባቸውን ተግባራት በሚገባ የማስተባበርና የማቀናበር ብቃት፣
➢ ችግሮችንና መፍትሄዎች የማስተሳሰር ብቃት፤	➢ በተቋም ደረጃ የሚለዩት ሪስኮች፣ የመፍትሄ አቅጣጫዎች፣ የተቋሙን ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታን የሚመልሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ ➢ በተቋም ደረጃ የሚለዩ ሪስኮች፣ የሚቀመጡት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ሁሉን አቀፍ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ ➢ የተለዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎች የሚያስገኙትን ትክክለኛ ጥቅም ማስላት፤ ➢ የተለዩ መፍትሄዎች የጎንዮሽ ጉዳት እንዳይኖራቸው ማረጋገጥ፤ ➢ እያንዳንዷን ሪስክ የመፍትሄ አቅጣጫ እንደተቀመጠላት ማረጋገጥ፤
➢ የማማከር ብቃት፤	➢ የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮችን በሳይበር ደህንነት ጉዳይ ማማከር፤
➢ በተለያየ አቅጣጫ የማየት ብቃት፤	➢ የሳይበር ደህንነት ስርዓት ቀረጻ እና ትግበራ ላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች (ከፖለቲካ፣ከኢኮኖሚ፣ማህበራዊ፣ ወዘተ..) በማየት ሁለንተናዊነትን በተላበሰ አኳሃን የመቃኘት፣ የመገንዘብ በኮምፒተንሲው ዙሪያም የማማከር ብቃት፤

3.2. የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ቡድን (ክፍል) የሥራ መደቦች

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ባለሙያ

ደረጃ: I

ዋና ዋና ተግባር እና ኃላፊነት	ዕውቀት	ክህሎት	የት/ደረጃ	ሥራ ልምድ	ሰርተፍኬቶች /ስልጠናዎች/
➢ ለንቃተ ህሊና ስልጠና ፕሮግራሞች የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ➢ የስልጠና እና ንቃተ ህሊና ፕሮግራም ስርዓት ንድፍ ለማዘጋጀት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት መረጃዎችን ያሰበስባል፤ ➢ አለማቀፋዊ፣ ቀጠናዊና ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ክስተቶች ላይ ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ➢ የንቃተ-ህሊና ማጎልበቻና ባህል መገንቢያ ፕሮግራሞችን ለመፈተሽ የሚያስችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ➢ ተቋማዊ የደህንነት አጠባበቅ መመሪያዎችን ይከታተላል፤ ያብራራል፤ ➢ ለተቋማዊ የንቃተ-ህሊናና ባህል ግንባታ ምዘና የሚያገለግሉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤	➢ የለሙ የንቃተ ህሊና እና ተቋማዊ ባህል ዳሰሳ ስርዓቶች ዕውቀት፤ ➢ የተለዩ የዳሰሳ መንገዶች እና ሰውን መመዘኛና የማብቂያ መንገዶች ዕውቀት፤ ➢ የተለዩ የትምህርት፣ ስልጠና፣ ንቃተ-ህሊናና የባህል ግንባታ አመራር ስርዓቶች ዕውቀት፤ ➢ የተለያዩ የንቃተ-ህሊናና ባህል ግንባታ ማዕቀፎችና ስርዓቶች ግንዛቤ፤ ➢ የተነደፉ የንቃተ-ህሊናና ባህል ግንባታ ስልት/ስትራቴጂዎች/ ግንዛቤ፤	➢ መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎት፣ የማዳመጥ እና ግብረ-መልስ የመቀበል ክህሎት፤ ➢ በሰው ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ የደህንነት ስጋቶች ቀድሞ የመረዳት ክህሎት፤ ➢ የተተነተኑ ሰውን የማበልጸጊያ መንገዶችን የመረዳት ክህሎት፤ ➢ ደህንነት ከሰው ጋር ያለውን መስተጋብር በመተንተን የመለየት ክህሎት፤	በኮምፒተር ሳይንስ፣ በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ፣በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ፤ ወይም በሳይኮሎጂ፣ በሶሺዮሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ፤	0-1	

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅም	ማብራሪያ
➢ በቡድን የመስራት ብቃት፤	➢ የተቋሙን ተልዕኮ ለመደገፍ፤ ግቦችን ለማሳካትና ለማጠናከር የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ፕሮግራም መገንዘብ፤
➢ ጥልቅ የንባብ ክህሎት፤	➢ ጥልቀት ያለዉ ዘርፈ ብዙ የንቃተ ህሊናና ባህል ማሳልበቻ ፅንሰ ሃሳቦችን፣ ማዕቀፎችን፣ ልምዶችንና ጥናቶችን አንብቦ በአውዳዊነት የመረዳት አቅም፤
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ ከስራ ባልደረቦቹና ከተቋሙ ሰራተኞች ጋር ተባብሮ መረጃዎችን የመሰብሰብ አቅም፤
➢ የመረጃ መተንተንና መተርጎም ብቃት፤	➢ አለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ሃገራዊ የሳይበር ደህንነት ክስተቶችን ተከታትሎ መረጃዎችን ተንትኖ የማቅረብ ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ፡ የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ባለሙያ
ደረጃ፡ II

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	ዕውቀት	ክህሎት	የት/ደረጃ	ሥራ ልምድ	ስርተፍኬቶች
➢ ለሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ስልጠና ፕሮግራሞች የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ትምህርት፣ ስልጠና እና ንቃተ-ህሊና ፕሮግራም ስርዓት ንድፍ ለማዘጋጀት የሚያስችል የዳሰሳ ሥራ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ➢ በሳይበር ደህንነት ፖሊሲ እና ፕሮሲጀር ገዢ ሰነዶች ላይ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ➢ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊናና ስልጠና ፕሮግራም ለማዘጋጀት የሚረዱ ግብዓቶችን ያሰባስባል፤ ➢ ሰራተኞች በተሰጣቸው የይለፍ (የፈቃድ) ደረጃ መጠን መብትና የተከለከሉትን ጉዳዮች መለየትና የይለፍ (የፈቃድ) ደረጃ እና ክልከላ ከመደረጉ በፊት ማብራሪያ ይሰጣል፤ ➢ የተቋሙ ሰራተኞች ያላቸውን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ደረጃ ለመገምገምና በውጤቱም መሰረት አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሰባስባል፤	➢ የለሙ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና የዳሰሳ ስርዓቶች ዕውቀት፤ ➢ የተለዩ የዳሰሳ መንገዶች እና ሰውን መመዘኛና የማብቂያ መንገዶች ዕውቀት፤ ➢ የተለዩ የሳይበር ደህንነት የትምህርት፣ ስልጠናና ንቃተ ህሊና አመራር ስርዓቶች ዕውቀት፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ማዕቀፎችና ስርዓቶች ግንዛቤ፤ ➢ የተነደፉ የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ስልት/ስትራቴጂዎች ግንዛቤ፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና በተቋም ውስጥ የመፍጠር እና የማሳደግ ግንዛቤ፤	➢ መሰረታዊ የተግባቦት ክህሎት፣ የማዳመጥ እና ግብረ-መልስ የመቀበል ክህሎት፤ ➢ በሰው ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ የሳይበር ደህንነት ስጋቶች ቀድሞ የመረዳት ክህሎት፤ ➢ የተተነተኑ ሰውን የማበልጸጊያ መንገዶችን የመረዳት ክህሎት፤	በኮምፒተር ሳይንስ፣ በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ፤ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ ወይም ሳይኮሎጂ፣ ሶሺዮሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ	ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ1-2 ዓመት፤ ለሁለተኛ ዲግሪ ከ0-1 ዓመት፤	

የመወዳደሪያ አቅሞች	ማብራሪያ
➢ በቡድን የመስራት ብቃት፤	➢ የተቋሙን ተልዕኮ ለመደገፍ፤ ግቦችን ለማሳካት እና ለማጠናከር የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ፕሮግራም መገንዘብ፤ ➢ የተቋሙን አውድ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሳይበር ደህንነት ባህል በተቋም ውስጥ በተጨባጭ ለመፍጠር ከተቋሙ ማህበረሰብ ጋር በቅርበት በቡድን የመስራት ብቃት፤
➢ የመግባባት እና የመቀናጀት ብቃት፤	➢ የተለያየ የሥራ ባህል እና የስራ ከባቢ፣ ማህበራዊ እምነት፣የትምህርት ድህረ-ታሪክ፣ የሙያ ድህረ-ታሪክ ያላቸው እና በተለያዩ እድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎችን በሙያዊ ስነ-ምግባር፣ በጥንቃቄ፣ ውጤታማነትን በሚያጎናፅፍ መልኩ እና መልካም ስነ-ምግባር በተላበሰ አኳሃን ተግባብቶ አብሮ ለመስራት የሚያስችል ብቃት፤
➢ የግንኙነት ብቃት፤	➢ የሳይበር ደህንነት ሁኔታን በተመለከተ መረጃውን ሊያውቁ ለሚገባቸው አካላት እንዲተላለፍ የማድረግ ብቃት፤ ➢ የሳይበር ደህንነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በሚኖሩ ውይይቶች እና ሌሎች ግንኙነቶች እራስን የመግለጽ ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ባለሙያ

ደረጃ: III

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	ዕውቀት	ክህሎት	የት/ደረጃ	ሥራልምድ	ሰርተፍኬቶች
➢ በተቋም ደረጃ አጀንዳና ይዘቶች/ዝርዝር/ ማኑዋሎችን ያለማል፣ ➢ አጀንዳዎች ተደራሽ የሚደረጉበት የግንኙነት ዘዴ ይወስናል፣ ➢ በተቋም ደረጃ ባህሪ/ባህል/ የፍላጎት ዳሰሳ ያከናውናል፣ ➢ ተቋማዊ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤ ➢ የስልጠና መንገዶችን ይለያል፤ ➢ የግምገማ ዳታዎችን ይተነትናል፤ ሰንዶ ያስቀምጣል፡ ➢ ተቋማዊ የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳዎችን ያከናውናል፣	➢ የተሰጠውን ችግር መሰረት በማድረግ የባህሪ/ባህል/ ዳሰሳ ለማከናወን የሚያስችል ግንዛቤ፤ ➢ የከባቢ ግንዛቤ፣ ለምሳሌ፡- ተቋማዊ ጉዳዮች፣ ተቋማዊ የአሰራር ስርዓቶች፣ ባህል፣ የግለሰብ ባህሪ፣ሃገራዊ ጉዳዮች(ሃገራዊ አጀንዳዎች)፣ የልማት እንቅስቃሴዎች፣ ባለድርሻ አካላት (አጥቂ፣ ተጠቂ)፤ ➢ የለውጥ/ግንባታ/ ግቦችን ግንዛቤ፤ ➢ የለውጥና የለውጥ አስተዳድር ግንዛቤ፤ ➢ የኢላማዎች (ተቋም፣ ግለሰብ፣ ቡድኖች፣ ወ.ዘ.ተ.) ግንዛቤ፤ ➢ የባህሪ/ባህል ለውጥ አላማና ግቦች ግንዛቤ፤ ➢ የባህሪ/ባህል ችግሮችን የመረዳት ብቃት፤ ➢ በተቋም ደረጃ ያሉ ባህሪ/ባህል ችግሮችን የመረዳት ብቃት፣	➢ ጥሬ ዳታ/ኢንፎርሜሽን/ ምንጭ በተለዩ ስርዓታዊ በሆኑ መንገዶች ግንኙነት፣ ምክንያትና ውጤትን፣ ክፍተትን የማወቅ፣ የመገምገም እና ዶክመንት የማድረግ፤ ➢ በደረጃው ምክረ ሃሳቦችን የመሰነድ፤ ➢ ከባቢ የመገንዘብና የመረዳት፤ ➢ የባህሪ/ባህል ለውጥ/ግንባታ ስልጠናዎች የመስጠት፤ ➢ የኮሙኒኬሽን ቻነል የመለየት የመምረጥ፤ ➢ የተነደፉ የባህሪና የባህል ግንባታ/ለውጥ መንገዶች/ እና ዒላማዎች የመለየት፣ በቅደም ተከተል (Priority) የማስቀመጥ ብቃት፤ ➢ አነስተኛ መጠን ያላቸው መፍትሄዎችን ዲዛይን የማድረግ ክህሎት፤ ➢ የራስ ስራን የማቀድ፣	በኮምፒተር ሳይንስ፤ በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በማናጅመንት በኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ወይም በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ፤ ወይም ሳይኮሎጂ፣ ሶሺዮሎጂ እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ፤	➢ ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ2-4 ዓመት የስራ ልምድ፤ ➢ ለሁለተኛ ዲግሪ 0-2 ዓመት በተንዳኝ የስራ መስክ የሰራ/ች፤	

			➢ ለራስ ስራ ዝርዝር ግቦችንና መለኪያዎችን የማውጣት፤ ➢ በደረጃው ስርአታዊ በሆነ መንገድ ሪፖርት የማድረግ፤ ➢ መልዕክት/ኢንፎርሜሽን/ ታዳሚን በሚመጥን ደረጃ በፅሁፍ/በገለፃ/ የማቅረብ ብቃት፤ ➢ መለስተኛ የኮምፒውተር ክህሎቶች፤ ➢ ከስራ አጋሮች ጋር ውጤታማ ግንኙነት የመፍጠር ክህሎት፤		

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅሞች	ማብራሪያ
➢ የግጭት አስተዳደር ብቃት (Conflict management)፤	➢ የሚለሙ ስትራቴጂዎች፣ ሞዴሎች፣ ሜተዶሎጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ማዕቀፎች እና ካሪኩለሞች ጋር የሚኖረውን መስተጋብር የመገንዘብና መፍትሄዎችን ዲዛይን የማድረግ ብቃት፣
➢ የማስተሳሰር (Alignment) ብቃት፤	➢ የተለዩ አጀንዳዎችና ኮንሰፕቶች ከኢላማዎች እንቅስቃሴ ጋር የማቆራኘት እና ትስስር የመፍጠር ብቃት፤
➢ ችግር የመፍታት ብቃት፤	➢ ችግሮችን የመለየትና የመተንተን፣ የኢንፎርሜሽን ትክክለኛነትና ጠቀሜታ የመመዘን፣ መፍትሄ የሚሆኑ አማራጮች የማፍለቅ እና የመገምገም፣ ምክረ-ኃሳብ የማመንጨት ብቃት፤

የሥራ መደብ መጠሪያ: የሳይበር ደህንነት ንቃተ-ህሊና ባለሙያ

ደረጃ: IV

ዋና ዋና ተግባርና ኃላፊነት	ዕውቀት	ክህሎት	የት/ደረጃ	ሥራልምድ	ሰርተፍኬቶች
➢ በተቋም ደረጃ የፍላጎት ዳሰሳዎችን ያዘጋጃል፣ ይመራል፤ ➢ የአጀንዳ/የኮንሰፕት/ መልዕክት ይዘት እንዲሁም ተደራሽ የማድረጊያ መንገድ ውጤታማነት ይገመግማል፤ ➢ የስልጠና መንገዶችን ዲዛይን ያደርጋል፤ ➢ ተቋማዊ ስልጠናዎችን ይመራል፤ ➢ ተቋማዊ የለውጥ ግምገማዎችን ይመራል፤	➢ የሚላማ ቀረጻ ዕውቀት፤ ➢ የኮሙኒኬሽን ፅንስ ሃሳብ የመተንተን (ዲዛይን) የማድረግ ዕውቀት፤ ➢ ላኪ-መልእክት ቻነል ተቀባይ (ግብረ-መልስ)፤ ➢ የተለዩ የግምገማ ስርዓቶች፣ስልቶችና መመዘኛዎች ዕውቀት፤ ➢ በተቋም ደረጃ ያሉ የባህሪ/ባህል/ ችግሮች ግንዛቤ፤ ➢ በተቋም ደረጃ ያሉ የባህሪ/ባህል ለውጥ/ ግንባታ ችግሮችን የመለየት፣ የመረዳትና የመተንተን፤	➢ የባህሪ/ባህል/ ለውጥ ኮንሰፕት የማልማት ብቃት፤ ➢ የባህሪ/ባህል ለውጥ የስልጠና ማንዋል የማልማት ብቃት፤ ➢ ተቋማዊ ትስስር የመፍጠር ክህሎት፤ ➢ ተቋማዊ ተፅእኖ የመፍጠር ክህሎት፤ ➢ በተቋም ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑ የባህሪ/ባህል ለውጥ/ግንባታ/ መንገዶችን ተግባራዊ ማድረግ፤ ➢ የባለድርሻ አካላት ፍላጎት የመረዳት ብቃት፣ የባለድርሻ አካላት ትንተና የማካሄድ ብቃት (ተሳታፊ ባለድርሻ አካላት)፤ ➢ ውጤታማ ተፅእኖ የመፍጠሪያ መንገዶች/ቻነሎች/ የመንደፍ፤ ➢ የተለየ ሚላማን የመገምገም ክህሎት፤ ➢ በተለዩ የግምገማ ስርአቶች መሰረት ከባቢ/ሚላማ/ ለውጥ የመገንዘብ፤ ➢ በየደረጃው ትምህርት የሚወሰድባቸውን ጉዳዮች ቀምሮ የመሰነድ፤	የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ በኮምፒተር ሳይንስ፤ በኮምፒተር ኢንጂነሪንግ፣ በማናጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ወይም ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ፤ ወይም ሳይኮሎጂ፣ ሶሺዮሎጂ እና ተመሳሳይ የሙያ ዘርፍ፤	➢ የመጀመሪያ ዲግሪ 4-6 ዓመት የስራ ልምድ፤ ➢ ሁለተኛ ዲግሪ 2-4 ዓመት የሥራ ልምድ	➢ CSAP (Certified Security Awareness Practitioner) (ቢኖር ይመረጣል)

		➢ በተቋም ደረጃ አጀንዳዎችን፣ ጭብጦችና ይዘቶችን ከኢላማዎች ጋር የማስተሳሰር፣ ➢ መፍትሄዎችንና አማራጮችን የማመንጨትና ዲዛይን የማድረግ፣ ➢ በተቋም ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎችን እና ግለሰባዊ ልዩነቶችን የመቀበል፣የማስተናገድ፤ ➢ በክፍል ደረጃ ካሉ አባላት ጋር ውጤታማ ግንኙነት የመመስረት ብቃት፣ ➢ ለሌሎች የቡድን አባላት ተገቢ የሆነ ድጋፍ የመስጠት ብቃት፣			

የመወዳደሪያ አቅሞች

የመወዳደሪያ አቅሞች	ማብራሪያ (Description)
➢ የግጭት አስተዳደር ብቃት (Conflict management)፤	➢ የሚለሙ ስትራቴጂዎች፣ ሞዴሎች፣ ፕሮግራሞች፣ ማዕቀፎችና ካሪኩለሞች የሚኖራቸውን መስተጋብር የመገንዘብና መፍትሄዎችን ዲዛይን የማድረግ ብቃት፣
➢ የማስተሳሰር ብቃት፣	➢ የተለዩ አጀንዳዎችን፣ ኮንሰፕቶችን ከኢላማዎች ጋር የማቆራኘት እና ትስስር የመፍጠር ብቃት፣
➢ ችግር መፍታት፤	➢ ችግሮችን የመለየትና የመተንተን፣ የኢንፎርሜሽን ትክክለኛነትና ጠቀሜታ የመመዘን፣ መፍትሄ የሚሆኑ አማራጮች የማፍለቅ እና የመገምገም፣ ምክረ-ኃሳብ የማመንጨት ብቃት፤
➢ ዕቅድና ቅንጅት፤	➢ ፍላጎቶችን በመለየት ዝርዝር ግቦችን ከዳር ማድረስ የሚያስችል ራስን ወይም ሌሎችን የሚያካትት ዝርዝር ተግባራትን የመቅረፅ እና የተግባራቱ አፈፃፀም ግቦቹን ለማሳካትና ለመከታተል የሚያስችል መመዘኛ ስርዓት የማበጀት ብቃት፤
➢ ተግባቦት፤	➢ ኢንፎርሜሽን እና ኃሳብ በብቃትና ግልፅ በሆነ በቃል እና/ወይም በፅሁፍ የማቅረብና የመግለፅ፤ ➢ ሌሎች የሚናገሩትን የማዳመጥ እና የመረዳት፤ ➢ ኢንፎርሜሽንንና ኃሳብን ለሌሎች የማጋራት ወይም ከሌሎች ጋር የመለዋወጥ፤ ➢ ሙሉ እና ጊዜውን የጠበቀ ወይም ታዳሚን ያገናዘበ ውሳኔ የመስጠት እና ሌሎች ሊስማሙበት በሚችሉበት መንገድ ኢንፎርሜሽንና ማቴሪያሎች የማቅረብ ብቃት፤
➢ ከሰዎች ጋር ግንኙነት የመፍጠር ብቃት፣	➢ የሌሎችን ስሜት፣ ፍላጎት እና አቅም የመገንዘብ እና ተገቢ ምላሽ የመስጠት፤ ➢ ምቹና ምቹ ባልሆነ ሁኔታ የሰዎችን ደረጃ፣ የስራ ሁኔታ፣ ወዘተ እንደ መመዘኛ ባለማስቀመጥ በብቃት ስራን የመስራት፣ የባህል እና ኢንተርፐርሰናል ልዩነቶችን የመቀበል፤ ➢ ግጭቶችና አለመስማማቶች ሲያጋጥሙ የተሳታፊዎቹ ስሜት እና ምላሽ መቆጣጠር በሚያስችል መንገድና በማለሰቦቹ የሚደርስ አሉታዊ ተፅእኖ በሚቀንስ አዎንታዊ በሆነ መንገድ የመፍታት እና ተገቢ የሆነ ድጋፍ የመስጠት ብቃት፤

